

# ክፍል ኣምስት

# የዘሬይቱ ኣውስትራሊያ

# የዛሬይቱ ኣውስትራሊያ

በዚህ ክፍል ስለ ኣውስትራሊያ ባህል፣ የፈጠራ ስዎችና የብሄራዊ ማንነት መማር ይችላሉ። ኣውስትራሊያ በዓለም ደረጃ የተከበረች ታታሪ የንግድ ስራ ሸሪክ ሃገር ናት። ኣውስትራሊያ ስደተኞች ለሃገሪቱ በቀጣይነት የሚያበረክቱትን የእድገትና የመታደስ ስራ ዋጋ ትሰጣለች።

## መሬቷ

የኣውስትራሊያ መሬት በዓለም ላይ ካሉት በጣም ጥንታዊ መሬቶች አንዷ ናት። በዓለም ካሉት ታላላቅ ሃገራት በስድስተኝነት የምትገኝ ሲሆን በዓለም ከሚገኙት ደሴቶች ሁሉ ደግሞ ትልቋ ደሴት ናት። በተጨማሪም በጣም ለጥ ያለች ሰው የሚኖርባት ደረቅ መሬት ናት። ኣብዛኛው የኣውስትራሊያ ምድር የተራቆተ ኣፈርና ዝቅተኛ የዝናብ መጠን ስላለው የእርሻ ስራን ከባድ ያደርገዋል። የመሃሉ ደረቅ ምድር ‘ምድረ በዳ /the outback/ የሚባል ሲሆን በጣም ሩቅና በጣም ከባድ ኣካባቢ ነው። በኣውስትራሊያ ውሃ በጣም ውድ ሃብት ነው።

ኣውስትራሊያ እንደዚህ ትልቅ ሃገር በመሆኗ ብዙ የተለያየ የኣየር ንብረት ያለባት ሃገር ናት። የምድር ወገብ ኣካባቢ የኣየር ንብረት ያላቸው በሰሜን ኣውስትራሊያ ምድረ በዳው ደግሞ በመሃል ይገኛል። በደቡብ በኩል ካለው በቀዝቃዛ ክረምት ጊዜ በረዶ ከተሸፈኑ ተራሮች ጀምሮ እስከ በጋው የንዳድ ማዕበል የሙቀት መጠኑ ይለያያል።

የኣውስትራሊያ መንግስት በዋናው ምድር ላይ ካሉት ስድስት መንግስታዊ /states/ እና ሁለት ክልላዊ /territories/ ኣስተዳደሮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ክልሎች ያስተዳድራል

- የኣሽሞርና ካርቲየር ደሴቶች
- ክሪስማስ ደሴቶች
- የኮከስ/ኪሊንግ ደሴቶች
- የጀርቪስ ቤይ ክልል
- የኮራል ባህር ደሴቶች
- የኣውስትራሊያ ኣንታርቲካ ክልል ሀርድና ማክዶናልድ ደሴቶች
- ኖር ፍሎክ ደሴቶች/ Norfolk Island።

## የዓለም ቅርስ ቦታዎች/ World Heritage sites

የሚከተሉት የኣውስትራሊያ የቅርስ ቦታዎች በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ ናቸው።

### ባህላዊ

- የኣውስትራሊያ የወንጀለኞች ማእከላት
- ቡጂ ቢም ባህላዊ ቦታ/ Budj Bim Cultural Landscape
- የሜልበርን ንጉሳዊ የኤግዚቢሽን ህንፃና የካርልተን የኣበባ ቦታ /Royal Exhibition Building and Carlton Gardens in Melbourne
- የሲድኒ ኦፔራ ሃውስ/Sydney Opera House።



የሲድኒ ኦፔራ ሃውስ /Sydney Opera House

## ተፈጥሯዊ

- በደቡብ ኣውስትራሊያና በኩንስላንድ የኣውስትራሊያ የኣጥቢዎች ቅሪት ማእከል/ Australian Fossil Mammal Sites in South Australia and Queensland (Riversleigh/Naracoorte)
- ክጋሪ/K'gari (ቅድም ክብል ብፍራሰር ደሴት ዝፍለጥ/formerly Fraser Island)
- ጎንድዋና የዝናባማ ደን በኣውስትራሊያ/Gondwana Rainforests in Australia
- ግሬት ባርየር ሪፍ/Great Barrier Reef
- ታላቁ የብሉ ማውንቴን ኣካባቢ/Greater Blue Mountains Area
- ሀርድና ማክዶናልድ ደሴቶች/Heard and McDonald Islands
- ሎርድ ሆዊ የደሴቶች ስብስብ/Lord Howe Island Group
- ማኳሪ ደሴት/Macquarie Island
- የኒንግሎ የባህር ዳርቻ/ Ningaloo Coast
- ፑርኑሉሉ/Purnululu ብሔራዊ መናፈሲ ቦታ
- የምዕራብ ኣውስትራሊያ የሻርክ ባህረ ሰላጤ/ Shark Bay, Western Australia
- የኩንስላንድ እርጥብ ሞቃታማ ቀጠና /Wet Tropics of Queensland።



በኣየርስ ዓለት ላይ የተገነባ የማእበል ቅርፅ ያለው የዓለት ስሪት በኡሉሩ-ኩታ ቱጁታ ብሄራዊ ፓርክ


## ቅይጥ/Mixed

- ካካዱ ብሄራዊ ፓርክ/Kakadu National Park
- የታዝማኒያጫካ/Tasmanian Wilderness
- የኡሉሩ ካታ ትጁታ ብሄራዊ ፓርክ/Uluru-Kata Tjuta National Park
- ዊላንድራ የሃይቅ ኣካባቢ/ Willandra Lakes Region።

እላይ ከተዘረዘሩት የምእራብ የምልክት ርእሶችና ኣስደናቂ የተፈጥሮ ሃብቶች፤ በሃገሪቱ የተለያዩ ኣካባቢዎች በተለይም ለኣቦርጅኖችና የቶረስ ስትሬት ደሴተኞች ላይ ከፍተኛ ኣስፈላጊነት ያላቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ቅዱሳን ቦታዎች ኣሉ። እነዚህ ቦታዎች ለኣውስትራሊያ ባህል ድርና ማግ ሲሆኑ ለሁላችንም ከፍተኛ ጠቀሜታ ኣላቸው። ቅዱሳን ቦታዎች ብዙ ጊዜ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር የታሪክ ትስስር ያላቸውና የታላቁን ምድር ባህላዊ እሴቶችን የዝምድና ግንኙነቶችና ማህበረሰባዊ ስርዓት ኣመላካች ናቸው።

# ሰፊ ኣገር

ኣቦርጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች ከምድሪቷ ጋር ልዩ ትስስር ኣላቸው። ከጎረቤቶቻቸው ላላቸው ግንኙነት ትልቅ ዋጋ የሚሰጡና ለመገናኘት ሲሉ በጣም ረጅም መንገድ ይጓዛሉ። የኣቦርጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች 'ፍኖተ ዘፈን/song-lines' ባህላዊ ህግን፣ ከመልክኣ ምድር የተያያዘ ታሪክና ባህል፤ በመላው ኣውስትራሊያ ከሚገኙት የባህልና የቋንቋ ቡድኖች ያላቸው ግንኙነት የሚገልፁ ናቸው። ለሺዎች ዘመናት እየተዘፈኑ ተጠብቀው የቆዩ ናቸው።



የታዝማኒያጫካ/Tasmanian Wilderness

በሌሎች የኣውስትራሊያ ኣካባቢዎች ብዙ ዋጋ ያላቸው የማይመስሉ እንደ ትምህርት፣ ጤናና የሱቆች የመሳሰሉ ኣገልግሎቶች በብዙ የኣውስትራሊያ ኣካባቢዎች በጣም ውስን ሆነው የሚገኝባቸው ቦታዎች ብዙዎች ናቸው። ኣገልግሎት በሌለባቸው ሩቅ ቦታ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ በጋራ መስራት ይጠበቅብናል። ታዋቂ ኣውስትራሊያውያን ሩቅ ቦታ በሚኖሩት ወገኖች ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት በከፍተኛ ብልህነትና የፈጠራ ስራዎች ሲረዱ ቆይተዋል።



## በእግር በማሽከርከር የሚሰራ ሬድዮ/ The pedal radio

በ1929, ኣልፍሬድ ትርሬጋር ከኣደላይድ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግር ማሽከርከር የሚሰራ ሬድዮ ነድፈዋል፡፡ ተጠቃሚዎች በእግሮቻቸው እየገፉ ባለ ሁለት ኣቅጣጫ ሬድዮ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ለየብቻ ተበታትነው የነበሩ መኖሪያ ቤቶች፣ በመስክ ስራ ለተሰማሩና የኣቦርጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች ከዚህ ፈጠራ ተጠቅመዋል፡፡ ይህ በእግር የሚዘወር ሬድዮ ሁለት ትላልቅ የኣውስትራሊያ ተቋማት እንዲቋቋሙ ረድቷል፣ ንጉሳዊ የበረራ ዶክተሮች ኣገልግሎትና /Royal Flying Doctor Service / እና School of the Air የሚባል የርቀት ትምህርት፡፡

## ንጉሳዊ የበረራ ዶክተሮች ኣገልግሎትና / Royal Flying Doctor Service

ኣባ ዮሃንስ ፍሊን/Reverend John Flynn በሩቅ ከሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ኣብረው በመኖር ሰርተዋል፡፡ ዶክተሮች በተቻለ ፍጥነት በኣየር ሩቅ ወዳሉት የገጠር ኣካባቢ በሽተኞች የማስመጣት ሃሳብ ነበራቸው፡፡ ይሄንን ለማድረግ መንግስት የኳንታስ ኣየር መንገድና የእርዳታ ቁሳቁሶች ተሰጣቸው፡፡ ንጉሳዊው የበራሪ ዶክተሮች ኣገልግሎት ከ1928 ጀምሮ ኣገልግሎት የጀመረ ቢሆንም ይሄንን ኣገልግሎት መጥራት የማይችሉ ብዙ የሩቅ ኣካባቢዎችም ነበሩ፡፡ በእግር የሚሰራው ሬድዮ መገኘት በጣም ተገልለው የሚኖሩ የህብረሰብ ክፍሎች ከሩቅ ዶክተር በመጥራት በተቻለ ፍጥነት ኣገልግሎት የሚያገኙበት ኣጋጣሚ ፈጠረ፡፡

## የርቀት ትምህርት/The School of the Air

እስከ 1950ዎቹ ድረስ በሩቅ ኣካባቢ ተለይተው የሚኖሩ ህፃናት በኣዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ትምህርታቸው በፖስታ እየተላከላቸው ይማሩ ነበር (ከላይ ፎቶግራፉን ይመልከቱ)፡፡ ኣደላይድ ሚትክ የሚባሉ የንጉሳዊው በራሪ ዶክተሮች ኣገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ደግሞ ይህ የሬድዮ ኣገልግሎት ሩቅ ቦታ ሆነው የሚማሩ ተማሪዎች ከኣስተማሪዎቻቸው ለመነጋገር ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ኣስተዋሉ፡፡ የኣሊስ ስፕሪንግ ኣገልግሎት የሁለት ኣቅጣጫ የኣየር ትምህርት በ1948 ተጀመረ፡፡ የኣየር የርቀት ትምህርቱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በወጉ ተጀመረ፡፡ የኣውስትራሊያ ልምድም በብዙ ሃገራት ተመሳሳይ መርሃ ግብር እንዲያካሂዱ ረዳ፡፡

ቀጥሎ ኣሮጌው የእግር ሬድዮ ከፍተኛ ፍሪኳንሲ ተቀባዮች ተተካ እሱ ደግሞ ኣሁን በኢንተርኔት ተተካ፡፡ የኣውስትራሊያ ንጉሳዊ የበራሪ ዶክተሮች ኣገልግሎትና የርቀት የኣየር ትምህርት ቤት በርቀት ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ትልቅ ጥቅም መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

# የኣውስትራሊያ ማንነት

የኣውስትራሊያ ማንነት በብዙ መንገዶች የተገነባ ሲሆን፤ ኣገር በቀል ውርሶችና ባህሎች፣ የህዝባችን ብዝሃነት፣ ታሪካችን፣ የያንዳንዱን ሰው ህይወት የሚመራው እሴታችን፣ የኑሮ ዘያችን እንዲሁም የምናደንቃቸውን ኣውስትራሊያውያንን ሁሉ ያካትተ ነው።

*ምዕራፍ 6, የኣውስትራሊያችን ታሪክ* ታሪካችን ላይ ያተኩራል። ቀደም ሲል የነበረውን የኣውስትራሊያ የቅኝ ኣገዛዝና የኣቦርጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች የፊትና የኋላ ታሪክ ያወሳል። ታሪኩ የኣውስትራሊያን ብዝሃነት፣ ህብረ ባህላዊ ማህበረሰብ፣ እንዲሁም ኣውስትራሊያ እንደ ኣንድ ሃገር በጋራ ስላጋጠሙን ተግዳሮቶችና ጦርነቶች ያካትታል።

የዚህ ምዕራፍ ማስታወሻ የምንከተለው የኑሮ ዘየና የምናደንቀው ህዝብ ላይ ያተኩራል።

## ስፖርትና መዝናኛ

ብዙ ኣውስትራሊያውያን ስፖርት ይወዳሉ እንዲሁም የኣውስትራሊያ የስፖርት ሰዎች በዓለም የውድድር መድረክ በጣም ኣስደናቂ ውጤት ኣግኝተዋል።

በታሪካችን ሁሉ ስፖርት የኣውስትራሊያ ህዝብ ባህርይ ሲቀይርና ህብረታችን ሲያጠናክር ቆይቷል። ከመጀመሪያው የሰፈራ ጊዜ ጀምሮ ስፖርት በገሃዱ ዓለም ከነበረው ኣስቸጋሪ የህይወት ጉዞ በሃሳብ የሚያመልጡበት መንገድ ሲሆን ቆይቷል። በጦርነት ጊዜም ቢሆን የኣውስትራሊያ የመከላከያ ሰራዊት ሊያጋጥማቸው ከሚችል ጭንቀት ለማላቀቅ የተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ሲያካሂዱ ነበር።

ስፖርት ለተጨዋቾቹም ሆነ ለተመልካቾቹ የጋራ መድረክ በመፍጠር ተሳታፊዎቹ በኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ የተካታችነትና ጠቃሚ የህብረተሰቡ ክፍሎች የመሆን ስሜት ይፈጥራል። የኣቦርጅንና የቶረስ የባህረ ሰላጤ ደሴተኞች እንዲሁም ሌሎች ስደተኞች በኣውስትራሊያ ውጤታማ የስፖርት ሰዎች ናቸው።

ብዙ ኣውስትራሊያውያን እንደ ክሪኬት፣ የቅርጫት ኳስ፣ የመረብ ኳስ /netball እና የገና ጨዋታ/ hockey የመሳሰሉ የስፖርት ውድድሮች ላይ ይሳተፋሉ። እንደ እግር ኳስ፣ ራግቢ ሊግ፣ ራግቢ ዩኒየን፣ እንዲሁም የኣውስትራሊያ ልዩ የሆነው የኣውስትራሊያ የእግር ኳስ ህግ (‘Aussie Rules’) የመሳሰሉት የተለያዩ የኳስ ደንብ ያላቸው ጨዋታዎች በተጫዋቾችም ሆነ በተመልካች በጣም ተወዳጅ የስፖርት ዓይነቶች ናቸው። ዋና፣ ቴንስ፣ ኣትሌቲክስ፣ ጎልፍ፣ ቢስክሌት መንዳት፣ የጫካ ጉዞ፣ በባህር ላይ ቆሞ መንሳፈፍ/ surfing፣ የበረዶ ላይ መንሸራተት ስኪንግ/skiing ተወዳጅ የመዝናኛና የስፖርት እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ኣውስትራሊያ በክሪኬት ጨዋታ በተለይ በጣም የሚያኮራ ውጤት ኣላት። የኣውስትራሊያና የእንግሊዝ ክሪኬት ቡድኖች ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ኣካባቢ ጀምሮ ባላንጣ ተፎካካሪ ሆነው ቆይተዋል።

የሜልበርን ዋንጫ “ ሃገሪቷን ቀጥ የሚያደርግ ውድድር/‘the race that stops the nation’ በዓለም ትልቁ የፈረስ ጉግስ ውድድር ነው። የመጀመሪያው የሜልበርን ዋንጫ የተካሄደው በ1861ዓ/ም ነው። የሜልበርን ዋንጫ የሚካሄደው የህዳር ወር በገባ የመጀመሪያ ሳምንት የሚከበር ሲሆን ከ1877 ጀምሮ ሲከበር ቆይቷል።

### ክቡር ጌታ ዶናልድ ብራድማን (1908–2001)



ሰር ዶናልድ ብራድማን በኣውስትራሊያ የኪሪኬት ጨዋታ ታሪክ በጣም ዝነኛው  የኣውስትራሊያ የስፖርት  ጀግና ናቸው። በቦውራል ኒው ሳውዝ ዌልስ የተወለዱና ለመጀመሪያ ጊዜ በ1928 ዓ/ም የክሪኬት ጨዋታ ተጫውተዋል።

በጣም የሚገርሙ ፈጣን ሯጭ ተጫዋች ነበሩ። በ1930 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እንግሊዝ ተጉዞ ባደረገው ውድድር ላይ ሁሉም በሚባል ደረጃ የመለጋት ክብረ ወሰኑን ሰብሯል። በ21 ዓመት እድሜው የኣውስትራሊያ እውቅ ተጫዋች ሆኗል። በ1948 ባደረገው የመጨረሻው ጉዞ ላይ ቡድኑ ‘የማይበገሩት/The Invincibles’ የሚባል ስም የተሰጠው ሲሆን ይህም ከእንግሊዝ ቡድን ጋር በተጫወቱባቸው ጨዋታዎች ሁሉ ኣንዴም ሳይሸነፉ በመጨረሳቸው ነው።

## ስነ ጥበብ

ኣውስትራሊያ የኣቦርጂኖችና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ባህልና ልምድ ያካተተ በጣም ደማቅ የስነ ጥበብ ትእይንት ኣላት። የኣውስትራሊያ ትእይንታዊና መድረካዊ የስነ ጥበብ ባለሞያዎች በፊልም፣ በስነጥበብ፣ በቲያትር፣ በሙዚቃ፣ በጭፈራ በኣውስትራሊያም ሆነ በባህር ማዶ ከፍተኛ ኣድናቆት ያስገኘ ነገር ነው።

### ስነ ፅሁፍ

ኣውስትራሊያ በጣም ጠንካራ የስነ ፅሁፍ ባህል ያላት ኣገር ናት። ይህም የሚጀምረው የኣቦርጂኖችና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች የተረት መንገር ጀምሮ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ኣካባቢ ወደ ኣውስትራሊያ ስለመጡት ወንጀለኞችን የቃል ታሪክ የቀጠለ ነው።

ኣብዛኛው የኣውስትራሊያ የመጀመሪያዎቹ ፅሁፎች ስለ ጫካውና በጣም ከባድ ስለሆነው ምህዳር ነበር። እንደነ ሄንሪ ላውሰንና ሚልስ ፍራንክሊን ስለ ኣውስትራሊያ ጫካዎችና ስለ ኣውስትራሊያ የኑሮ ሁኔታ ግጥም ፅፈዋል።

ሌሎች ዝነኛ የሆኑት ታዋቂ የዘመኑ ደራሲያን ፒተር ኬሪ፣ ኮሊን ማክካሎ፣ ሳሊ ሞርጋን፣ ቲም ዊንተን፣ ቶም ኪናሊና ብርይስ ኮርትንይ።

### ጁዲ ሪይት (1915–2000)

ጁዲ ራይት በጣም ልዩ ገጣሚ፣ ወግ ኣጥባቂ እንዲሁም ለኣውስትራሊያ ኣቦርጂኖች ነፃነት ኣቀንቃኝ ነበረች። ስለኣውስትራሊያና ህዝቧ ያላትን ፍቅር በግጥሞቿ ገልፃዋለች። የኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካና የንግስቷ የወርቅ ሜዳሊያን ጨምሮ በጣም ብዙ ዓለም ዓቀፍ ሽልማቶችን ኣግኝታለች። በተጨማሪም የኣውስትራሊያ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ኮሚቴ ኣባልነትና የኣቦርጅኖች ድርድር ኮሚቴ ኣባል ነበረች።

ጁዲ ራይት በነበራት የግጥም ችሎታናና የኣውስትራሊያ ስነፅሁፍና በማህበራዊና ምህዳራዊ ለውጥ መነቃቃት ባደረገችው መነቃቃት ትወሳለች።



### ትያትርና ፊልም

የኣውስትራሊያ ተውኔቶች፣ ፊልሞችና ፊልም ሰሪዎች በኣውስትራሊያና በውጭ ሃገር ተቀባይነት ኣላቸው። እንደ ኬት ብላንከት፣ ጀፍሪ ራሽ፣ ኒኮል ኪድማን ኣንድ ሂው ጃክማን የመሳሰሉት ኣውስትራሊያዊ ተዋንያን እንዲሁም እንደ ፒተር ዊርና ባዝ ላርማን የመሳሰሉት የፊልም ሰሪዎች ዓለም ኣቀፍ የልቀት ሽልማት ተሸላሚ ሆነዋል።

### የሚታይ ስነጥበብ

በጣም ትልቅ እውቅና የተሰጠው የኣውስትራሊያ የሚታይ ስራ ድንቅ የሆነው የሃገር በቀል የስእል ስራዎችና እንዲሁም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሮበርትስ፣ ፍሬደሪክ ማክ ኩቢንእና ኣርተር ስትሪተን ትላልቅ የጫካ ገፅታ የስእል ስራ ታዋቂ ሰዎች ናቸው። በ20ኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ላይ ሩሰል ድራይስዴል /Russell Drysdale  እና ሲድነ ኖላን /Sidney Nolan/ በተባሉት ተዋናዮች የገጠሩን አስቸጋሪነት በደማቅ ቀለም ገልፀውታል። በቅርቡ ጊዜ ብረት ዋይትሊ /Brett Whiteley/ ልዩና ግልጽ ዘይቤው በዓለም አቀፍ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቷል። በኣልበርት ነምጅራ ኤምሊ ካም ኪንግዋረይ፣ ሮቨር ቶማስና ክሊፎርድ ፖሰም ቲያፓልጂሪ የተሰሩ ሃገር በቀል የስነጥበብ ስራዎች በኣውስትራሊያና በውጭ ኣገር በጣም ተፈላጊዎች ናቸው።

### ሙዚቃና ጭፈራ

በአውስትራሊያ የሙዚቃ ድምጽ ዲጅሪዱ /didgeridoo/ በመባል የሚታወቀው የጥንት የአውስትራሊያ ነዋሪዎች የሙዚቃ መጫወቻ በተቀዳሚነት የሚጠራ መሳሪያ ነው።

ኣውስትራሊያውያን በሁሉም የሙዚቃ ዘርፎች የታቀፉ፤ ላቅ ያለ የሙዚቃ ችሎታ ያላቸውና የለስላሳ የሙዚቃ መሳሪያ፣ በሃገረሰብና በዘመናዊ የሮክ ሙዚቃና ብዙ ኣስተዋፅ ኦ ኣድርገዋል።

ካይሊ ሚኖግ /Kylie Minogue/፣ ጂሚ ባረንስ /Jimmy Barnes/፣ ፖል ከሊ /Paul Kelly/፣ ኦሊቭ ኒውተን ጆን /Olivia Newton-John/፣ ጆን ፋርናም /John Farnham/፣ ኒክ ኮቭ /Nick Cave/፣ እንዲሁ ከጥንታዊ ኣውስትራሊያያንም እንደ ኣርኪ ሮች /Archie Roach/፣ ጋሩሙል /Gurrumul/ እና ጀሲካ ሟቦይ /Jessica Mauboy/ የመሳሰሉ በጣም የታወቁት የኣውስትራሊያ ሙዚቀኞች ናቸው። እንደ AC/DC እና INXS ያሉት የሙዚቃ ባንዶችም በዓለም ኣቀፍ ደረጃ ብዙ ተከታዮች ያፈሩ ናቸው።

የአውስትራሊያ ዳንስ እያደገ የመጣው እንደ ሰር ሮበርት ሄፕማን /Sir Robert Helpmann/፣ ሜሪል ታንካርድ /Meryl Tankard/ እና ስቴፈን ፔጅ /Stephen Page/ በመሳሰሉት ታላላቅ ጨፋሪዎችና የዳንስ ኣቀናባሪዎች ነው። ባንጋራ የኣቦሪጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች የጭፈራ ካምፓኒ ሲሆን ልዩ በሆነ የዳንስ ዓይነቱና የድምፅ ቀስቃሽ ሙዚቃና ንድፉ በዓለም ኣቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅና ኣግኝቷል።

## ሳይንሳዊ ግኝቶችና ፈጠራዎች

አውስትራሊያውያን በመድሃኒት፣ በቴክኖሎጂ፣ በእርሻ፣ በማእድን አወጣጥና በፋብሪካ ውጤት ስራ ላይ ጠንካራ ታሪክ ኣላቸው።

በሳይንስና በህክምና የፈጠራ ስራዎች ብዙ አውስትራሊያኖች የኖቤል ሽልማት አግንተዋል።

በተጨማሪም በሳይንስ ጥሩ ውጤት ላስገኙትም የዓመቱ አውስትራሊያዊ የሚባል ሽልማት ያገኛሉ። በ2005 ዓ.ም ሽልማቱ ለፕሮፌሰር ፊዮና ውድ /Professor Fiona Wood/ እንደተሰጠና ይህም ለተቃጠሉ ሰዎች ህክምና የሚረዳ በቆዳ ላይ የሚረጭ መድሃኒት ስላገኙ ነው። በ2006 ዓ.ም ሽልማቱ ለፕሮፌሰር ኢያን ፍሬዘር /Ian Frazer/ ለማህጸን ነቀርሳ መከላከያ የሚሆን ክትባት ስላገኙ ነው። በ2007 ዓ.ም ሽልማት ላይ ደግሞ የአካባቢ ሳይንስ ተመራማሪ ለሆኑት ፕሮፌሰር ቲም ፍላነርይ /Tim Flannery/ ሽልማቱን ኣግኝተዋል።

ፕሮፈሶር ውድ /Professor Wood/ እና ፕሮፌሰር ፍሬዘር /Professor Frazer/ ሁለቱም ከብሪቴን ወደ አውስትራሊያ የመጡ/የተሰደዱ ናቸው። ፕሮፌሰር ፍሬዘር /Professor Frazer/ የፈጠራ ስራው ረዳት የነበሩት ዶ/ር ጂያን ዝሁ /Dr Jian Zhou/ ቀጣዩ ትሽላሚ ሲሆኑ እሳቸውም ከቻይና የተሰደዱና ከዚያም የአውስትራሊያ ዜግነት ያገኙ ነበሩ።

### ዶ/ር ፊዮና ዉድ እም (1958 ተወለዱ)



ዶ/ር ዉድ አዳዲስ ቴክኒኮችን ከሚጠቀሙ፣የተከበሩ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች እና ተመራማሪ አውስትራሊያዊያን አንዷ ናቸው። በፕላስቲክ እና በዳግም ግንባታ ቀዶ ሕክምና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው እውቅ የዓለማችን የቃጠሎ ጉዳት ልዩ ሐኪም ሲሆኑ በቃጠሎ ምክንያት በሚመጣው ጉዳት ልዩ ሃኪም፣ ተመራማሪ እና ቴክኖሎጂውን በማፍለቅ ረገድ ፈር ቀዳጅ ናቸው።

በ2002 የባሊ የቦምብ ፍንዳታ ጉዳተኞችን በማከም ያበረከቱት አስተዋፅዖን ተከትሎ ዶ/ር ዉድ "Member of the Order of Australia " በመባል የተጠሩ ሲሆን በ2003 ይህ ከፍተኛ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በቃጠሎ ጉዳት የተጠቁትን በህክምና የመንከባከብ ሥራቸው እውቅና ያገኘው የዓመቱ አውስትራሊያዊ ሰው ተብለው በ2005 ሲመረጡ ነው።

## ፕሮፌሰር ፍሬድ ሃሎውስ (1929–1993)

ፕሮፌሰር ፍሬድ ሃሎውስ ሞያቸውን በጣም የሚያፈቅሩ የዓይን ሃኪም ሲሆኑ በኣውስትራሊያና በዓለም ከኣንድ ሚልዮን ሰዎች በላይ የዓይን ብርሃናቸውን የመለሱ ሰው ናቸው። ፍሬድ ሃሎውስ የተወለዱት በኒውዝላንድ ነው። በ1965 ወደ ኣውስትራሊያ ከመጡ በኋላ በሲድኒ ሆስፒታል የዓይን ህክምና መምሪያ ሃላፊ ሆኑ።

በሁሉም ሰዎች እኩልነት የሚያምኑ ናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የኣቦሪጅኖች የህክምና ኣገልግሎት የመሰረቱ ሲሆን በኣሁኑ ጊዜ በተለያዩ የኣውስትራሊያ ኣካባቢዎች በብዛት ይገኛሉ።

በ1980 ፍሬድ ሃሎውስ በዓለም ዙሪያ ባሉት ታዳጊ ሃገሮች በመዘዋወር የዓይን ህክምና ማእከላት ኣቋቁመዋል። በሚያዝያ 1989 ዓ/ ም የኣውስትራሊያ ዜግነት ኣገኙ።

የፕሮፌሰር ሃሎው መልካም ስራ ፍሬድ ሃሎውስ ፋውንዴሽን /Fred Hollows Foundation/ በሚል ድርጅት ስም ስራውን ቀጥሏል።



# የዓመቱ ኣውስትራሊያዊ

ከ1960 ጀምሮ የዓመቱ ኣውስትራሊያዊ የሚባል ሽልማት የተጀመረ ሲሆን በየዓመቱ በኣስተዋፅኦቸው የመሪነት ተግባር ላከናወኑ ኣውስትራሊያውያን የሚሰጥ ሽልማት ነው። ማንም ሰው ከየትኛውም ኣካባቢ ለዚህ ሽልማት መጠቆም ይችላል።

የኣመቱ ኣውስትራሊያዊ ተብለው ሽልማት የሚያገኙት ሰዎች በዘመኑ በስራቸው ከሌላው በልጠው ሃገራቸውን ላገለገሉ ሰዎች ይሰጣል። ምርጥ ሃሳባቸውን በማጋራትና ተግዳሮት በመፍጠር የተሻለች ኣውስትራሊያን እንድንፈጥር የራሳቸውን ኣስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸው።

ሽልማቱ የሚያካትተው የዓመቱ ወጣት ኣውስትራሊያዊ፣ የዓመቱ ኣዛውንት ኣውስትራሊያዊና የዓመቱ የኣካባቢ ጀግና ኣውስትራሊያዊን ያካትታል።

በኣሁኑ ወቅትና በፊት ጊዜ ሽልማቱን ያገኙት ሰዎች ዝርዝር በሚከተለው ድረ ገፅ ማግኘት ይችላሉ። www.australianoftheyear.org.au.

## ዶ/ር ጀምስ ማኪ /Dr James Muecke AM

**የኣይን ቀዶ ጥገናና የኣይነ ስውርነት መከላከያ እውቅ ሃኪም**
**የ2020 ዓ/ም የኣውስትራሊያ የዓመቱ ሰው በመሆን ተመርጠዋል**

ዶ/ር ማኪ ማየት ለሁሉም /Sight For All/ የሚለውን የበጎ ኣድራጎት ድርጅት ከመሰረቱት ሰዎች ኣንዱ ሲሆኑ ዋና ዓላማውም ኣይነ ስውርነትን ለማጥፋት የሚረዱ ምርምሮች፣ ተቋሞች፣ ከሌሎች ሃገራት ጋር በመሆን ስልጠናዎችን መስጠት ነው።

እንደ ዶ/ር ማኪ ዓይነ ስውርነት የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ስለሆነ ሁሉም ሰው ማየት የሚችልበት ዓለም መፍጠር ነው።



## ፕሮፌሰር ሚችል ሲሞንስ (በ1967 ተወለዱ)

**የኳንተም ፊዚክስ ፕሮፌሰር**
**የ2018 የዓመቱ የአውስትራሊያ ሰው**

ፕሮፌሰር ሲሞንስ በአውቶሚክ ኤሌክትሮኒክስ እና በኳንተም ስሌት ፈር ቀዳጅ ናቸው። እሳቸው ‹‹በኮምፒውተር ዘመን የህዋ እሽቅድድም›› ብለው በሚጠሩት ግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑት ፕሮፌሰር ሲሞንስ በሺ የሚቆጠር አመታት ይፈጅ የነበረውን ስሌት በኳንተም ኮምፒውተር አማካኝነት በደቂቃዎች መፍትሔ ማግኘት እንዲችል ኣድርገዋል። ይህ ግኝት በመድሐኒት አሰራር፣ የኣየር ንብረት ትምበያ፣ያለ ሹፌር የሚንቀሳቀስ መኪና፣ኢተፈጥሮአዊ የማሰብ ችሎታ እና ሌሎች ግኝቶች ላይ ስር-ነቀል ለውጥ እንዲኖር እገዛ አድርጓል።

በኳንተም መረጃ ሳይንስ ሥራቸው ላበረከቱት አስተዋፅዖ በ2018 ፕሮፌሰር ሲሞንስ የዓመቱ አውስትራሊያዊ ተብለው ተመርጠዋል። በ2019 ‹‹በሳይንስ ትምህርት አገልግሎት የኳንተም እና አውቶሚክ ኤሌክትሮኒክስ መሪ እንዲሁም ለሌሎች ተምሳሌት የሆኑ በሚል እውቅና›› የአውስትራሊያ ከፍተኛ ሽልማት ተሸልመዋል።



# የኣውስትራሊያ ገንዘብ/ምንዛሪ

በኣውስትራሊያ የገንዘብ ምንዛሪ ሳንቲሞችና የዶላር ኖቶች ለኣውስትራሊያ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሰዎችና ምልክቶች ያሳያሉ።

በገንዘቡ ላይ እንዲታዩ የሚደረጉት ሰዎች በአውስትራሊያ ታዋቂ ዝነኛ የሆኑትና በማሕበራዊ ለውጥ፣ ሳይንስ፣ ፖለቲካ፣ በውትድርና አፈጻጸም እና በስነጥበብ ተነሳሽነትና ተሰጥዎ የነበራቸው ናቸው።

## ንግሥት ዳግማዊት ኤልሳቤት (1926–2022)

ንግሥት ኤልዛቤት ዳግማዊ የአውስትራሊያ ርዕሰ አስተዳደር መንግሰት ነበረች። የአውስትራሊያና የዩናይትድ ኪንግደም ንግሥት ነበረች። ረጅምና ተወዳጅ በነበረው የግዛት ዘመኗ ሁሉ ጠንካራና የተረጋጋች ነበረች።




## የፓርላማ ህንፃና የፊት ለፊት መግቢያ የጠጠር ስእሎች

የፓርላማው ህንፃ ንድፍ ፕላን የተመሰረተው ከመሬቱ ኣቀማመጥ በተያያዘ ሲሆን ይህም በፓርላማው ምክር ቤት የህንፃ ባለስልጣን የወጣ ነው። የፊት ለፊት መግቢያ የጠጠር ስእሎች በማእከላዊ ኣውስትራሊያ ያለውን በረሃ መሰረት ያደረገው ‘የፖሰምና የዋላቢ ህልም /Possum and Wallaby Dreaming/። በሚል ርእስ በማይክል ኔልሰን ጃጋማራ የተሰራ ነው።




## ዴም ሜሪ ጊልሞር /Dame Mary Gilmore (1865–1962)

ዴም ሜሪ ጊልሞር ደግሞ ሌላ ደራሲ፣ ጋዜጠኛ፣ ገጣሚና የማህበራዊ ለውጥ ቀስቃሽ ናቸው። ሴቶችን፣ ድሃ ሰዎችንና ኣቦርጅኖችንና የቶረስ ባህረሰ-ላጤ ደሴተኞችን በመወከል ስትፅፍና ስትናገር በመኖራቸው ይታወሳሉ።




## ኤቢ ባንጆ ፓተርሰን /AB ‘Banjo’ Paterson (1864–1941)

ኣንድሪው ባርተን ፓተርሰን ገጣሚ፣ የዘፈን ደራሲና ጋዜጠኛ ነበሩ። በ‘ባንጆ’ ስም ነበር የሚፅፈው ፓተርሰን /Waltzing Matilda/ በሚል የደረሰው በህዝብ ከፍተኛ ተወዳጅነት ባለው የህዝብ ዘፈን በተለይ ይታወሳል።




## ኣባ ጆን ፍሊን /Reverend John Flynn (1880–1951)

በዓለም የመጀመሪያውን የአየር ወለድ ህክምና አገልግሎት፣ ንጉሳዊ የበራሪ ዶክተር አገልግሎት በኣውስትራሊያን የጀመሩ ናቸው። በአውስትራሊያ ገጠር አካባቢ የህክምና አገልግሎትን በመጀመር የብዙ ሰዎች ህይወት በማዳናቸው ይታወሳሉ።



## ሜሪ ሬበይ /Mary Reibey (1777 – 1855)

ሜሪ ሬበይ /Mary Reibey/ በኒው ሳውዝ ዌልስ ቅኝ ግዛት ውስጥ ሀሳብ በማመንጨት ለሴት ነጋዴ መንገድ ቀዳጅ ነበሩ። አውስትራሊያ በኣስራዎቹ ዓመታቸው ሰፋሪ በመሆን እንደገቡ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከበሩ መሪ ሆኑ።




## ኢዲዝ ኮዋን /Edith Cowan (1861 – 1932)

ኢዲዝ ኮዋን የማሕበራዊ ሠራተኛ፣ ፖለቲከኛና ለሴቶች እኩልነት መብት ተከራካሪ ነበሩ። የመጀመሪያዋ የአውስትራሊያ የፓርላማ ኣባል ሆነው የተመረጡ ሴት ነበሩ።




## ዴቪድ ዩናፖን /David Unaipon (1872 – 1967)

ዴቪድ ዩናፖን ፀሃፊ ህዝብ ፊት ተናጋሪና ኣዲስ ነገር ፈጣሪ ነበሩ። በሳይንስና በስነፅሁፍ እንዲሁም የኣቦርጂኖችና የቶረስ ስትሬት ሰዎች የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል ይታወሳሉ።




## ሰር ጆን ሞናሽ /Sir John Monash (1865–1931)

ሰር ጆን ሞናሽ መሃንዲስ፣ ኣስተዳዳሪ እንዲሁም በጣም ዝነኛ የወታደራዊ መሪ ነበሩ። በነበራቸው የመሪነት ብቃት፣ ስለላና ኣንደበተ ርቱእነት ይታወሳሉ።




## ዴም ኒል መልባ /Dame Nellie Melba (1861–1931)

ዴም ኒል መልባ በዓለም ከፍተኛ ዝና የነበራት ድምፃዊት/ዘፋኝ በዓለም ደረጃ የዘፈን ንግስት በመባል የምትታወቅ ስትሆን በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ታዋቂነት የነበራት ኣውስትራሊያዊ ዘፋኝ ናት።



# ብሄራዊ በዓላትና ኣከባበራቸው

የኣውስትራሊያ ብሄራዊ በዓላት የኣውሮፓውያን መስፈር የበዓላት ኣከባበርና ታሪካዊ ኣመጣጥን ያንፀባርቃል።

## ቋሚ ቀናት

- **የአዲስ ዓመት ቀን ጥር/January 1** አዲስ ዓመት መጀመሪያ ይከበራል።
- **የአውስትራሊያ ቀን ጥር/January 26** ይህንን የሚከበርበት ምክንያት አውስትራሊያዊነት ምን ማለት እንደሆነ ለማንፀባረቅ፣ ዘመናዊቷን ኣውስትራሊያን ለማክበርና የጋራ ታሪካችንን ቅቡል ለማድረግ ነው። ቀኑ የሚያስታውሰው በ1788 ዓ.ም የመጀመሪያው ጦር መርከቦች በሲድኒ ሰርጥ የገቡበትን ቀን ለማስታወስ ነው።
- **የአንዛክ/Anzac Day ሚያዚያ/April 25** በአንደኛ የዓለም ጦርነት ጊዜ የአውስትራሊያና የኒው ዚላንድ የጦር ኮሮች ጋሊፖሊ/Gallipoli ላይ ያረፉበትን ቀን ያስታውሳል። ይህ በዓል በዚህ ጊዜ የሰላም ማስከበር ስራ ላይ በማገልገል ለነበሩ ለሞቱ አውስትራሊያኖች በሞላ በፅሞና የምናስታውስበት ቀን ነው። በተጨማሪም በተለያዩ የጦር ኣውድማዎች የሚሳተፉትን ወንድና ሴት የሰራዊት ኣባላት ያላቸውን ጀግንነትና ቆራጥነት ለማክበርም ጭምር ነው።
- **የገና ቀን/Christmas Day ታህሳስ/December 25** ጌታ እየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን በመሆኑ ስጦታ የሚሰጥበት ቀን ነው።
- **የቦክስሲንግ ቀን/Boxing Day ታህሳስ/December 26** ከገና በዓል ጋር ተያይዞ የሚከበር በዓል ነው።

## ተለዋዋጭቀናት

- **የወዛደር ቀን/Labour Day ወይም የስምንት ሰዓት ቀን/Eight Hour Day** የሚከበረው በአውስትራሊያ ሠራተኞች በቀን የስምንት ሰዓት ሥራ ስለማሸነፍ የሚከበር ነው። በዓለም የመጀመሪያ የሆነ።
- **ፋሲካ/Easter** የጌታ እየሱስ ክርስቶች የሞትና ትንሳኤ የሆነውን የክርስቲያን ታሪክ መታሰቢያ ለማክበር ነው።
- **የንጉሡ ልደታ ቀን የሚከበረው** በአውስትራልያ ርዕሰ መስተዳድር ንጉሥ ሳልሳዊ ቻርልስ/ King Charles III ልደት ስም ነው። ይህ ክብረ በዓል በሰኔ/June ወር በሁለተኛውሰኞ ቀን ከዌስተርን አውስትራሊያ ና ከኩንስላንድ በስተቀር በእያንዳንዱ መንግስታዊና ክልላዊ መስተዳድር ይከበራል።

## ሌሎች ህዝባዊ በዓላት

እነዚህ ህዝባዊ በዓላት በተለያዩ መንግስታዊና ክልላዊ መስተዳድሮችና ከተማዎች ይከበራሉ። ለምሳሌ፡ በአውስትራሊያ ዋና ከተማ ክልላዊ ኣስተዳደር የካንበራ ቀን/Canberra Day አለው፣ ደቡብ አውስትራሊያ የፈቃደኞች ቀን/Volunteers Day ሲኖረው እንዲሁም ዌስተርን አውስትራሊያ ደግሞ የመስራች ቀን/Foundation Day ህዝባዊ በዓላት ሆነው ይከበራሉ።

## ሌሎችጠቃሚ ቀናት (በዓላት ያልሆኑ)

- **የስምምነት ሳምንት** መጋቢት 21ጨምሮ ለኣንድ ሳምንት የሚከበርሲሆን ይህም ብዝሃ ባህላችን የምናከብርበር ነው።
- **የአውትራሊያ ዜግነት ቀን በመስከረም** 17 የሚከበር ሲሆን ይህም የአውስትራሊያ ህዝብ ያለውን የጋራ ማስተሳሰሪያችን የሆነውን የ ኣውስትራሊያ ዜግነት የምናከብርበትና እያንዳንዳችችን ሃገር በበጋራ ለመገንባት ላይ ያለን ሚና ለማንፀባረቅ ነው።
- **ብሄራዊ የእርቅ ሳምንት/National Reconciliation Week / የሚከበረው ከግንቦት 27 እስከ ሰኔ 3** ሲሆን በሃገራችን ፍትህ፣ እኩልነት፣ ኣንድነትና የጋራ መከባበር ኣሸናፊ ሆኖ የሚወጣባት ኣገር እንድትሆን ለምናደርገው ጥረት ማሳያ ነው።

# የኣውስትራሊያ ህዝብ

ኣውስትራሊያ በዓለም ደረጃ የተደባለቀ ማህበረሰብ ብዝሃነት ካሏቸው ሃገራት ኣንዷ ናት። ከሃገሪቱ ጠቅላላ ህዝብ ውስጥ ወደ ሶስት በመቶ የኣቦሪጂኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች ናቸው። ከጠቅላላው ህዝብ ሩብ ያህል በውጭ ሃገር የተወለደ ሲሆን ከ200 ሃገራት በላይ በስደት የመጣ ነው። የኣውስትራሊያ ህዝብ ብዝሃነት ሃገሪቱ በቋንቋ፣ በእምነት፣ በባህልና ልምድ የበለፀገች እንድትሆን ኣድርጓታል።

የጋራ ብልፅግና ሃገራት ኣባል በመሆኗ ምክንያት ኣውስትራሊያ ከዩናይትድ ኪንግዶም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ኣላት።

የኣውስትራሊያ ህዝብ የኣውስትራሊያ ዜግነትን በታላቅ ኩራት ይመለከቱታል። ይህም ብዝሃነት በኣንድነት የሚያስተሳስር ጥምረት ስለሆነ ነው። የኣውስትራሊያ የዜግነት ቀን በየዓመቱ መስከረም 17 ቀን ይከበራል። ይህ ቀን ሁሉም የኣውስትራሊያ ዜጎች በሃገር ግንባታና የሃገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ መልክ የማስያዝ ሚና የምንጫወትበትን ያንፀባርቃል።

# የኣውስትራሊያ ኢኮኖሚ

አውስትራሊያ የተረጋጋና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ያላት ስትሆን፣ ንቁና በሙያ ለተካኑ ሠራተኞቻችን ክብርና ዋጋ እንሰጣለን፡፡ ስዎች በአውስትራሊያ ውስጥ ያላቸው የኑሮ ደረጃ ጥራት በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ካላቸው ሃገሮች አንዷ ያደርጋታል፡፡

## ዲክ ስሚዝ Dick Smith (በ1944 ተወለደ)

ዲክ ስሚዝ ኣንዱ የኣውስትራሊያ ባለሃብት ነጋዴ ሲሆን ተጋፋጭና ትልቅ የበጎ ኣድራጎት ሰው ነው፡፡ ሃብቱ በኤለክትሮኒክስ እቃዎች ንግድ የተመሰረተና በሃብቱም ኣውስትራሊያ እንድትበለፅግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በኣውስትራሊያ ብቻ የሚሰሩ የምግብ ኩባንያዎች የጀመረ ሲሆን፤ በኣውስትራሊያውያን ባለቤትነት የሚሰሩትን ለማገዝ በጣም ብዙ ሚልዮን ዶላሮችን ኣውጥቷል፡፡

በ 1986 ዓ/ም የዓመቱ ኣውስትራሊያዊ ሰው ሆኖ የተመረጠ ሲሆን ለቴክኒካዊ እድገትና ለኣካባቢ ምህዳር ጥበቃ ያደረገው ኣስተዋፅኦም ሽልማት ኣግኝቷል፡፡ በኣውስትራሊያና በታዝማኒያ መካከል ያለውን ባህር በኣየር ፊኛ የተሻገረ የመጀመሪያ ሰው ነው፡፡ በደፋር መንፈሱ፣ በንግድ ስራ ስኬቱና በሃገር ወዳድነቱ የታወቀ ሰው ነው፡፡



## ግብይት

በአውስትራሊያ የተረጋጋና ዘመናዊና የፋይናንስ ተቋማት ሲኖሩ የታክስና የንግድ ሥራ እንቅስቃሴን ህግጋት በማስጠበቅ የንግድ እንቅስቃሴው በማያሰጋ ሁኔታ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ የአገልግሎት ኢንዱስትሪዎች ማለት ቱሪዝም፣ ትምህርትና የፋይናንስ አገልግሎት በአውስትራሊያ ጠቅላላ ሃገራዊ ምርት (GDP) የሚያበረክተው ኣስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

የአውስትራሊያ ኢኮኖሚ መረጋጋት ኢንቨስተሮች ከተለያየ ሃገር እንዲመጡ ያደርጋል፡፡ የአውስትራሊያ ሽቀጥ/ኣክሲዮን የሽያጭ ገበያ ከኤሽያ-ፓስፊክ/ Asia- Pacific ክልል በትልቅነታቸው ከሚታወቁት ኣንዱ ነው፡፡

## ንግድ

አውስትራሊያ የንግድ አጋሮች ቻይና/ China፣ ጃፓን/Japan፣ ዩናይትድ ስቴትስ/ United State፣ ሳውዝ ኮሪያ/ South Korea፣ ኒውዚላንድ/ New Zealand እና ዩናይትድ ኪንግደም/ United Kingdom ናቸው፡፡ ኣውስትራሊያ በብዛት ወደ ውጭ ለንግድ የምታቀርበው የከሰል፣ የብረት መኣድን፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ጋዝ ትምህርትና የቱሪዝም ኣገልግሎት ናቸው፡፡ ለኣውስትራሊያ የኢኮኖሚ እድገት ዋናው ኣስተዋፅኦ ኢኮኖሚው ለንግድ ክፍት መደረጉ ነው፡፡

## የመኣድን ማውጣት ስራ

አውስትራሊያ እንደ ድንጋይ ከሰል፣ መዳብ፣ ፈሳሽ የተፈጥሮ የመኣድን ኣሸዋ የበለፀገች ሃገር ናት፡፡ እነዚህም በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው ናቸው፡፡

# ኣውስትራሊያ እንደ ዓለም ኣቀፍ ኣባል

አውስትራሊያ በዓለም ኣቀፍ ኣባል ነት ያላት ሚና በጣም ያኮራታል። ኣውስትራሊያውያን ይሄንን ሚናቸውን ሌሎች በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ያልበለፀጉትን ሃገሮች በመርዳት ያሳያሉ።

## ዓለም አቀፋዊና የሰብዓዊ እርዳታ ጥረት

የኣውስትራሊያ መንግስት ዓለማቀፍ የእርዳታ ፕሮግራም ያልበለፀጉ ሃገሮች ድህነታቸውን ለመቀነስና ለዘላቂ ልማት በሚያደርጉት ጥረት ብዙ ድጋፍ ኣድርጋለች። ይህ የድጋፍ ሲሰጥ የነበረው በቅርበት ላይ ላሉና በተለያዩ የዓለም ኣካባቢ ላሉት ህዝቦች በመንግስቶቻቸው በኩል ነው።

ኣውስትራሊያ በውጭ አገር አደጋ ሲፈጠር አውስትራሊያኖች ከፍተኛ ልግስና ኣሳይተዋል። በኣውስትራሊያ የእርዳታ ፕሮግራም በኩል በቀጣይነት ችግር ለሚያጋጥማቸው አገሮች በየወቅቱ እርዳታ ሲሰጥ ቆይቷል።

በ2018 ዓ/ም ዶ/ር ሪቻርድ ሃሪስ እና ዶ/ር ክሬግ ቻለን የኣውስትራሊያ ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ የጀግንነት ሽልማት፣ የጀግንነት ኮከብ፣ ከሌሎች በኣውስትራሊያ የተፈቀዱ ሜዳይ (OAM)፣ በታይላንድ የዋሻ የጎርፍ ኣደጋ በ12 ታዳጊ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ላይ ሲደርስ እነዚህን ልጆች ለማዳን በወሰዱት ጥረት ነው።

## በዓለም ኣቀፍ መድረክ ያለው ንቁ ተሳትፎ

የተባበሩት መንግሥታት (UN) በ1945 ዓ.ም ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ አውስትራሊያ ትሳታፊ አባል ናት። ኣውስትራሊያ በ1951 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው የስደተኞች ህግ መሠረት፤ መስፈርቱን ላሟሉ ሰዎች አውስትራሊያ የጥገኝነት መብታቸውን ታስጠብቃለች። በተጨማሪም በተባበሩት መንግሥታት ሰላም የማስከበር ጥረት እንዲሁም በታዳጊ ሃገራት ለሚከሰቱት የሰብዓዊ ቀውስና የድንገተኛ ኣደጋ ጊዜ አስተዋጽኦ ታደርጋለች። በተጨማሪም በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ከፍተኛ ተሳትፎ ታደርጋለች።

በ1971 ዓ.ም አውስትራሊያ የኢኮኖሚ ትብብርና እድገት ድርጅት (OECD) ሙሉ አባል ሆናለች። የድርጅቱ/OECD ዓለም ኣቀፍ ንግድ በማስፋፋት በተለያዩ ሃገራት ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊና ደህንነት ለማምጣት ነው።

አውስትራሊያ በእስያ-ፓስፊክ ክልል ውስጥ ካሉት ሃገራት በቅርብ በመተባበር ትረዳለች።፣ በእስያ-ፓሲፊክ ሃገራት የኢኮኖሚ ትብብር፣ የምስራቅ እስያ ከፍተኛ ጉባኤ እንዲሁም ኤፓሲፊክ ደሴቶች መድረክ ንቁ ኣባል ነች። የደቡብ እስያ ሃገራት የውይይት ኣጋርና በኣካባቢው መድረክ ተሳታፊ ናት።

### ዶ/ር ካትሪን ሃምሊን /Dr Cathrine Hamelin AC (born 1924–2020)



ዶር ካትሪን ሃምሊን የማህፀን ስፔሻሊስት የነበሩ ሲሆን በኢትዮጵያ እድሜ ልካቸውን የሚሰቃዩትን ወጣት ሴቶችን ሲረዱ ኖረዋል። ከ1959 ዓ/ም ጀምረው ዶር ሃምሊን ኣዲስ ኣበባ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ወጣት ሴቶች በወሊድ ምክንያት ለሚደርስባቸው 'obstetric fistula' የሚባል ጉዳት በማከም ነው። የዚህ ዓይነት የውስጥ ጉዳት ያለባቸው ሴቶች ሽንታቸውን መቆጣጠር ባለመቻላቸው ምክንያት በጣም ተዋርደውና ከህብረተስቡም ተገልለው ይኖራሉ።

ዶ/ር ሃምሊን እና ባላቸው የኣዲስ ኣበባን ፊስቱላ ሆስፒታልን መሰረቱ። ጥረታቸው ውጤትም በሺ የሚቆጠሩ ሴቶች ጤንነታቸው ተጠብቆ ወደ መደበኛው የኑሮ ህይወታቸው መመለስ ነው።

በ1995 ዶ/ር ሃምሊን Companion of the Order of Australia, የሚባለውን የኣውስትራሊያ ከፍተኛው ሽልማት ኣግኝተዋል።

# የኣውስትራሊያ ኖቤል ሎሪየቶች /Australian Nobel Laureates

ኣውስትራሊያ በህክምና ሳይንስ ምርምር የታወቀች ናት። ቀጥሎ የተዘረዘሩት አውስትራሊያውያን በዚህ መስክ የኖቤል ሽልማት ኣግኝተዋል።

- ፕሮፌሰር ዊልያም ብራግ Professor William Bragg (1862 – 1942) እና ሎረንስ ብራግ/ Lawrence Bragg (1890 – 1971) የፊዚክስ ሊቃውንት
  ዊልያም ብራግ (አባት) እና ሎረንስ ብራግ (ወንድ ልጅ) በ1915 ዓ.ም የፊዚክስ ተደናቂ ሽልማት አሸናፊ ሲሆኑ ይህ 'በራጂ ምርመራ/X-rays አድርጎ ግልጽ ትንታኔ ስለማድረግ ላደረጉት አገልግሎት'።
- ሰር ሃዋርድ ዋልተር ፍሎሪ/ Sir Howard Walter Florey (1898 – 1968) የበሽታ ተመራማሪ/Pathologist ነበሩ
  በአደላይድ በሳውዝ አውስትራሊያ የተወለዱ ሲሆን፣ ሆዋርድ ፍሎረይ በፊዝዮሎጂ ወይም ሕክምና በመመራመር ለብዙ ተላላፊ በሽታ ፈዋሽ የሆነውን ፔኒሲሊን የተባለን መድሃኒት' በ1945 ዓ.ም (በጣምራ) በማግኘት ታዋቂነት አግንተዋል።
- Sir Frank Macfarlane Burnet (1899 – 1985) የህክምና ሳይንቲሰት እና በሰነ ህይወት /Scientist and Biologist ተመራማሪ ነቸው
  በቪክቶሪያ ውስጥ ተወለዱ፣ ፍራንክ በርነት/Frank Burnet 'የበሽታ መከላከል ሀይል ለመቋቋም መድሃኒት በማግኘታቸው' በ1960 ዓ.ም (በጣምራ) በ በስነ ግብረ ኣካል/Physiology ወይም በመድሃኒት ታዋቂነት ሽልማት አግንተዋል።
- ሰር ጆን ካረው ኤክለሰ Sir John Carew Eccles (1903 – 1997)
  በስነ ግብረ ኣካል ባለሙያ ሲሆኑ በመልበርን ውስጥ እንደተወለዱና 'በሰውነት ነርቭ የህብረ ዋህስ ማእከልና ሽፋን ዙሪያ ያለን የአሰራር ችግር በማግኘታቸው' በ1963 ዓ.ም (በጣምራ) 'በስነ ግብረ ኣካል/Physiology ወይም በመድሃኒት ታዋቂነት ሽልማት አግንተዋል።
- በጀርመን የተወለዱት ሰር በርናንድ ካትዝ/Sir Bernard Katz (1911–2003),ሃኪምና ህወታዊ-ስነኣካል/ biophysicist
  በ1941የኣውስትራሊያ ዜግነት ኣገኙ። በ1970 ከስርዓተ -ነርቭ የተያያዘ 'በነርቭ ጫፎች የሚገኙ ቁስ ኣካላዊ ኣስተላላፊዎችና የሚከማቹበት፣ የሚለቀቁበትና የሚያንቀላፉበት ስርዓት"/ discoveries concerning the humoral transmitters in the nerve terminals and the mechanism for their storage, release and inactivation'/ የሚባል የምርምር ውጤት በማግኘታቸው ምክንያት በህክምና ፊዝዮሎጂ የኖቤል ሽልማት ኣግኝተዋል።
- ፕሮፌሰር ጆን ዋርክካፕ ኮርንፎርዝ / Professor John Warcup Cornforth (1917 – 2007)
  በስድኒ ውስጥ እንደተወለዱና 'በስተሪዮ ኬሚስትሪ ስለ ንጥረ ነገሮች ውህድነት ኬሚካላዊ ለውጥ ላደረጉት ሥራ' በ1975 ዓ.ም (በጣምራ) በኬሚስትሪ ታዋቂነት ሽልማት አግኝተዋል።
- ፕሮፌሰር ፒተር ዶይቲ/Professor Peter Doherty (በ1940 ዓ.ም ተወለዱ) የበሽታ መከላከያ ባለሙያ/Immunologist
  Peter Doherty በኩንስላንድ ውስጥ እንደተወለዱና 'በተለይ ስለ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ተከላካይ ሴል በተመለከተ ላስገኙት ጥሩ ውጤት' በ1996 ዓ.ም (በጣምራ) በስነ ግብረ ኣካል ወይም በመድሃኒት ታዋቂነት ሽልማት አግንተዋል።
- ፕሮፌሰር ባሪ ማርሻል/Professor Barry Marshall (በ1951 ዓ.ም ተወለዱ) የሆድ ውሰጥ እቃ ባለሙያ/ Gastroenterologist እና ዶክተር ሮቢን ዋረን/Doctor Robin Warren (በ1937 ዓ.ም ተወለዱ) የበሽታ ባለሙያ/Pathologist
  ፕሮፌሰር ባሪ ማርሻል/Barry Marshall እና Robin Warren በጋራ ሆነው 'ስለ ባክቴሪዩም ሄሊኮባክተር ፒሎሪ /bacterium Helicobacter pylori ችግርና ስለ ሚያስከትለው የጨጓራ በሽታና የምግብ መፍጨት ቁስለት በሽታን በማወቃቸው' በ2005 ዓ.ም በስነ ግብረ ኣካል Physiology ወይም በመድሃኒት ታዋቂነት ሽልማት አግንተዋል።
- Professor Elizabeth Helen Blackburn (በ1948 ዓ.ም ሲወለዱ) የባዮሎጂ/Biologist ሊቅ ናቸው
  ኤልዛበት ብላክበርን የተወለዱት በሆባር/Hobart ውስጥ ሲሆን ይርኖብል ሽልማት ያገኙት በፊዚዮሎጂ ወይም በ2009 ዓ.ም ከህክምና ጋር 'ባደረጉት ምርምር ጥናት ሲሆን እንዴት የተሎመርስ እና የተሎማርስ ኢንዛይም ንጥረ ነገሮች የክሮሞሶምስ ውህደትን እንደሚከላከሉ ይሆናል'። እንዲሁም አውስትራሊያ በስነ-ጽሁፍ አንድ ታዋቂ ማእረግ አለ።
- ፕሮፌሰር ብሪያን ፕ ሽሚት (በ1967) የተወለዱ የሰነ ከዋክብት
  ኣጥኚ ሲሆኑ 'ከርቀት ሆኖ የከዋክብት ፍንዳታ በመመልከት የዩኒቨርስ የመስፋፋት ፍጥነት የመረዳት ግኝት/ the discovery of the accelerating expansion of the universe through observations of distant supernovae'/ በሚል ከዩኒቨርስ መስፋት ጋር በተያያዘ ላደረጉት ግኝት (በጋራ ) በ2011 ዓ/ም የፊዚክስ ሽልማት ኣሸናፊ ሆነዋል።

ቀጥሎ የተመለከቱት ኣውስትራሊያዊ በስነፅሁፍ ኣሸናፊ ሆነዋል።

- ፓትሪክ ኋይት/ Patrick White (1912 – 1990) የኖቭል ተሸላሚና የቲያትር ደራሲ ነበሩ
  አውስትራሊያዊ ከሆኑ ወላጆች ለንደን ውስጥ ተወለዱ፤ ፓትሪክ ኋይት 'አዲስ አርእስት የሆነውን የጀግንነት ግጥምና ስሜት ቀስቃሽ ደራሲ በመሆናቸው' በ1973 ዓ.ም በስነ-ጽሁፍ ደራሲ ታዋቂነት ሽልማት አግንተዋል።



# ምዕራፍ ስድስት

# የኣውስትራሊያ ቀን

# የኣውስትራሊያ ቀን

የኣውስትራሊያ ታሪክ በተለያዩ ህዝቦችና ክስተቶች ቅርፅዋን ይዛለች።

## ስለ ኣቦርጅኖችና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች /Aboriginal and Torres Strait Islander peoples/

ኣቦርጅኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች በዓለም በጣም ጥንታዊና እስካሁን ቀጣይነት ያለው ባህልና ልምድ ያላቸው ቀደምት የኣውስትራሊያ ነዋሪዎች ናቸው።

የመሬት ውስጥ የቅርስ ጥናት/ኣርኪዮሎጂ እንደሚያመለክተው ኣቦሪጂን ህዝቦች ከ65,000 እስከ 40,000 ዓመታት በፊት ወደ ኣውስትራሊያ እንደመጡ የሚያመለክት ሲሆን እነሱ ግን የዚች ምድር የፍጥረት ታሪክ ማእከል እንደሆኑና የመፈጠራቸው ታሪክ የተጀመረውም ይህች ምድር ስትፈጠር ጀምሮ እንደሆነ ያምናሉ።

ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች እድሜ ጠገብ እምነትና ባህል ያላቸው ሲሆን እስከ ኣሁን ድረስም ይመሩበታል ከምድሪቱ ጋር በጣም የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውና ታሪካቸው፣ ስነ-ጥበባቸውና ጭፈራቸው የተያያዘ ነው።

### ቋንቋዎች

ከብሪታንያ ሰፋሪዎች በፊት በኣቦሪጅኖችና ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ከ700 በላይ ቋንቋዎችና የአነጋገር ዘይቤዎች ይጠቀሙ እንደነበር ነው። በአሁኑ ጊዜ ወደ ከ100 የሚሆኑ ቋንቋዎች ጥቅም ላይ ይገኛሉ፤ ነገር ግን ከ20 የማይበልጡ ናቸው ወደ ቀጣይ ትውልድ እየተሸጋገሩ ያሉት። በኣፈ ታሪክ የሚነገሩ የአገሬው ተወላጅ ባህሎች እጅግ አስፈላጊ ሲሆኑ፤ ምክንያቱም ስለ ህዝብና መሬቷ ታሪክ ስለሚናገሩ ነው።

### የህልሙ ዓለም

የህልሙ ዓለም የሚባለው የኣቦሪጅንና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች እውቀታቸው፣ እምነታቸውና ተግባራቸውን የሚመሩበት መንገድ በምእራባውያን የሚገለፅበት ኣባባል ነው።

የህልሙ ዓለም ታሪክ ህፃናት ከወላጆቻቸውና ከሃገር ሽማግሌዎች የሚነገራቸው ታሪኮች ናቸው። እነዚህ ታሪኮች መሬታቸው እንዴት እንደተሰራችና ሰዎች እንዴት እንደሰፈሩባት ያተኩራል። ታሪኮቹ ለህፃናቶቹ በጣም ጠቃሚ የሆነ የተግባር ትምህርት ያስተላልፋሉ ለምሳሌ በጫካው ምግብ የት እንደሚገኝ ይጠቁማሉ።

የህልሙ ዓለም ታሪኮች የሚነገሩትም በሙዚቃ፣ በዘፈንና በጭፈራ ነው። የኣቦሪጅንና የቶረስ ስትሬት ደሴተኛ ህዝቦች ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ከቀደምት ኣባቶቻቸው ያላቸውን ጥልቅ ቁርኝት ያጣጥማሉ።

ጥንታዊው የባላገሮች ስነጥበብ ኣለት በመቅረፅ፣ ወይም ስዕልና የመሬት ንድፍ ነበር። የማእከላዊ ኣውስትራሊያ ሰዎች በተለይ ትእይንታዊ ስነጥበብ በነጠብጣብ፣ በክብና ሌሎች ከመሬትና ከህልሙ ዓለም ጋር የተያያዙ ባህላዊ ምልክቶች ሲጠቀሙ፤ ወደ ሰሜን ኣካባቢ ያሉት ደግሞ የስእል ጥበባቸው ከሰው፣ ከእንስሳና ከመንፈሳዊ ምልክቶች ጋር የተሳሰረ ነው።

የህልሙ ዓለም ኣሁንም ለኣቦሪጅን ህዝቦች በጣም ጠቃሚ ባህል ነው።



የካካዱ ኣቦሪጅኖች ስነ ጥበብ

# የመጀመሪያዎቹ የኣውሮፓውያን ሰፋሪዎች በኣውስትራሊያ

## ቀደምት የኣውሮፓውያን ኣሰሳ

በ17ኛው ክፍለ ዘመን የኣውሮፓ ኣሳሾች ‘Terra Australis Incognita’ ወይም ያልታወቀው የደቡብ ምድር ብለው የጠሩት ኣንድ ክፍል ኣገኙ። በ1606 ዊልያም ዣንስዙን / Willem Janszoon የሚባል የዳች ሰው በኣውስትራሊያ ሰሜናዊ ጫፍ በምዕራብ ኬፕ ዮርክ ባህረገብ መሬት ላይ ካርታ ሰራ። በዚህ ዘመን ኣካባቢ የስፔን መርከበኛው ልዊዝ ቫኤዝ ደ ቶረስ /Luís Vaez de Torres/ በባህር ወሽመጡ በኩል ወደ ሰሜናዊ ኣውስትራሊያ ተጓዘ።

ከ1600ዎቹ የዳች ባህረኞች የምዕራብ ኣውስትራሊያን ኣሰሰው ካገኙ በኋላ ኣካባቢውን ንው ሆላንድ /‘New Holland’/ ብለው ጠሩት።

በ1642 ኣቤል ታዝማን የኣዲሷ ምድር ዳርቻ ኣገኘ ስሟንም /‘Van Diemen’s Land’/ ብሎ ጠራት (ኣሁን ታዝማኒያ የሆነችው)። በሺዎች የሚቆጠር የኣውስትራሊያ ዳርቻዎች ካርታም ሰራ። ጨርሶ ያልሰራውን የኒው ሆላንድ ካርታ የሚያሳየው መሬቱ በሰሜን በኩል ከፓፓዋ ኒው ጊኒ ጋር እንደተያያዘ ነው።

ዊልያም ዳምፒየር ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የኣውስትራሊያን መሬት የረገጠ እንግሊዛዊ። በ1684 በሰሜናዊ ምዕራብ ዳርቻ በኩል ነበር ያረፈው። በነበረው ከፍተኛ ድርቅና የኣቧራ ብዛት ኣንፃር ኣንፃር ይህ ኣገር ለመስፈርም ሆነ ለንግድ ሊውል ይችላል ብሎ ኣላሰበም።



የኣቤል ታዝማን የኒው ሆላንድ ካርታ 1644

## ካፒቴን ጀምስ ኩክ

በ1770 ዓ/ም ጀምስ ኩክ የቢባል እንግሊዛዊ ወደ ኣውስትራሊያ ምስራቃዊ ዳርቻ እስኪደርስ ሌላ ኣውሮፓዊ ይሄንን ቦታ ኣላገኘውም ነበር። ኩክ በእንግሊዝ መንግስት ወደ ደቡባዊ ፓሲፊክ ለኣሰሳ የተላከ ልኡክ ነበር። የምስራቃዊ ዳርቻ ካርታ እየሰራ ኢንዶቨር ቦታኒ ቤይ ላይ ከዘመናዊው ሲድኒ ኣጠገብ መርከቡን ኣሳረፈ። ጀምስ ኩክ ይህንን ቦታ ኒው ሳውዝ ዌልስ ብሎ ጠራውና የንጉስ ጆርጅ ሳልሳዊ ግዛት መሆኑን ኣሳወቀ።

## ፍርደኞችን ማጓጓዝ

አብዛኛው የመጀመሪያዎቹ የአውሮፓውያን ሰፋሪዎች ፍርደኞች በመሆናቸው አውስተራሊያን ልዩ ሃገር ያደርጋታል። አሜሪካ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ታላቋ ብሪታኒያ ፍርደኞችን ወደዚያው ስለማትልክ የብሪታኒያ እስር ቤቶች በጣም ተጨናነቁ። ታላቋ ብሪታኒያ በ1786 የተወሰኑትን ፍርደኞች አዲሷ ቅኝ ግዛትዋ ወደ ሆነችው ኒው ሳውዝ ዋልስ ለማጓጓዝ ወሰነች።

## የመጀመሪያው ቅኝ ግዛት

የመጀመሪያው የኒው ሳውዝ ዌልስ ቅኝ ግዛት አገረ ገዢ ካፒቴን አርተር ፊሊፕ ነበሩ። የመጀመሪያዎቹ 11 የጦር መርከቦችን እየመሩ ከብሪታንያ ወደ ሌላው የዓለም ክፍል የሆነው የሲድኒ ሰርጥ ጥር 26 ቀን 1788 ዓ.ም. ያለ አንዳች ችግር ደረሱ። ይህንን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ የአውስትራሊያ ቀን ይከበራል።

## የመጀመሪያዎቹ የሰፈራ አመታት

ቅኝ ገዢዎች የሰፈሩበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በጣም አስጨናቂ ነበሩ። ሕብረተሰቡ እንዳይራብ አገረ ገዢው ፊሊፕ እያንዳንዱ ሰው እሳቸው እና ሰራተኞቻቸውን ጨምሮ ተመሳሳይ መጠን ያለው ቀለብ እንዲሰፈር አደረጉ። የእሳቸው ቀናነት እና ውሳኔ የቀኝ ገዢዎች የመጀመሪያዎቹ የጭንቅ ዓመታትን እንዲያልፉ ረዳቸው።



ከብሪታንያ የተነሱት የመጀመሪያ መርከቦች በ1788
በሲድኒ ሰርጥ የደረሱበት።

ፍርደኞች በመጀመሪያዎቹ የሰፈራ ጊዜያት ጠንክረው ሠርተዋል የእስር ጊዜኣቸውን የጨረሱ ነፃ ሴቶች እና ወንዶች በመሆን ወደ ማሕበረሰቡ ተቀላቅለው አስፈላጊ ስራ በመስራት ቤተሰብ ለመምራት እንዲችሉ ተደርጓል።

## የተለዩ ምቹ አጋጣሚዎች

በአውስትራሊያ ይኖሩ የነበሩት የቀድሞው አውሮፓውያን በአብዛኛው የእንግሊዝ፣ ስኮቲሽ፣ ወሊሽ እና አይሪሽ ህዝቦች ናቸው። ስኮቲሽ፣ ወሊሽ እና አይሪሽ ምንም እንኳን ከእንግሊዝ ጋር ጦርነት ላይ የነበሩ ቢሆንም አራቱም ህዝቦች በአውስትራሊያ ተቀራርበው በጋራ አብረው ይሰራሉ።

ፍርደኞች እና ከእስር የተለቀቁ ግለሰቦች በቅኝ ግዛቱ ምቹ አጋጣሚዎችን ይፈልጉ ጀመር። ከእስር ከተለቀቁት የተወሰኑቱ ተንቀሳቅሰው በራሳቸው የንግድ ስራ ጀመሩ። ሌሎቹ በግብርና፣ በንግድ፣ በሱቅ እና በህትመት ስራ ላይ ተሰማርተው ጥሩ ስራ ሰርተዋል።

### ካሮላይን ቺዝም (1808-77)

ካሮላይን ቺዝም ቀዳሚ የማሕበራዊ መስተጋብር ማሻሻያ ያከናወኑ ሲሆን በተለይም ያላገቡ ሴቶች በቀድሞው ቅኝ ግዛት ሁኔታዎች እንዲሻሻሉላቸው አድርገዋል። በ1838 ከወታደራዊ አዛዥ ባለቤታቸው እና ከአምስት ልጆቻቸው ጋር ሆነው ወደ አውስትራሊያ መጡ። በሲድኒ ጎዳናዎች ላይ ይኖሩ የነበሩትን ስደተኛ ሴቶችን ረድተዋል። በጥቂት ዓመታት ውስጥ 16 የስደተኛ ሴቶች ማረፊያ ቤቶችን በቅኝ ግዛቱ ስር አቋቋሙ።

በመርከብ ወደ ቅኝ ግዛቶች ይመጡ የነበሩ ግለሰቦች ምቾታቸው ተጠብቆ እንዲጓጓዙ ካሮላይን ጠንክረው ሰርቷል። ጥገኝነት እና ድህነትን ከምስኪኖች ለማስወገድ ይቻል ዘንድ የብድር አቅርቦት ዕቅድ ተለሙ።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ የአውስትራሊያ ትምህርት ቤቶች በካሮላይን ቺዝም ተሰይመው ይጠራሉ። ስደተኞችን አዲስ ሕይወት እንዲኖራቸው ለመርዳት ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የስደተኛ ጓደኛ በመባል ይታወሳሉ።



## አገረ ገዢ ማኳሪ

ማኳሪ እንዲሁም አገረ ገዢው ፊሊፕ እና አገረ ገዢው ላችላን ትልቅ ታሪካዊ ዱራ ይዘው ይገኛሉ። የኒው ሳውዝ ዌልስ አገረ ገዢ በነበሩበት ከ1810 እስከ 1821 ከፍርደኞች የፀዳ የቅኝ ግዛት ሰፈራ አቋቋሙ። የግብርና ስራን አሻሻሉ፣ አዳዲስ መንገዶችንና የሕዝብ መገልገያዎችን ሰሩ፣ እንዲሁም አውስትራሊያ እንድትስፋፋ እገዛ አበረከቱ።

አገረ ገዢው ማኩሬ ለትምህርት ገንዘብ በጀቱ የቀድሞ ፍርደኞችን መብትም እንዲጠበቅ አደረጉ። የተወሰኑትን የቀድሞ ፍርደኞች ለስራ በማሰማራት የዳኝነት እና የመንግስት ሰራተኛነት ስራ ሰጡአቸው።

በቅኝ ግዛቱ ጥሩ ለውጥ በማምጣታቸው የተነሳ አገረ ገዢው ማኩሬ በታሪክ የተከበሩ ናቸው። በኒው ሳውዝ ዌልስ በስማቸው የተሰየመ ዩኒቨርሲቲ አለ።

## የፍርደኞች ቅርስ

የአገረ ገዢው የሥልጣን ደረጃ ለአንድ ግለሰብ ያደላ ስለነበረ ቀጣዩ የቅኝ ግዛቱ አገረ ገዢ ለማማከር እና ማሻሻያ ለማድረግ በ1823 የኒው ሳውዝ የሕግ አውጪ ምክርቤት ተመሰረተ።

ታላቋ በሪታኒያ ፍርደኞችን ወደ ኒው ሳውዝ ዌልስ በ1840፣ ታዝማኒያ በ1852 እንዲሁም ወደ አውስትራሊያ በ1868 መላክ አቆመች። በአጠቃላይ ከ160,000 በላይ ፍርደኞች ወደ ውስትራሊያ ተልኳል። በነዋሪዎች እና ከእስር ከተፈቱ መካከል የነበረው ልዩነት ቀስ በቀስ ጠፋ። በ1850ዎቹ ቅኝ ገዢዎች በራሳቸው አስተዳደር ስነምግባር ያለው ማህበረሰብ ለመገንባት ፈለጉ። ብዙ የአውስትራሊያ ዜጎች ከፍርደኞች የዘር ሐረግ ስላላቸው ኩራት ይሰማቸዋል።

### አቦሪጂናል እና ቶሬስ የአውሮፓ ሰፋሪዎች ከመጡ በኋላ ጠባብ የባህር ወሽመጥ ደሴት ነዋሪዎች ሆነዋል

በ1788 የመጀመሪያዎቹ የአውሮፓ ሰፋሪዎች በመጡ ጊዜ ከ750,000 እስከ 1.4 ሚልዮን የሚደርሱ አቦሪጂናል እና ቶሬስ የባህር ወሽመጥ ደሴትኛ ህዝቦች በአውስትራሊያ ይኖሩ ነበር። ይህ 250 የሚደርሱ የተለያዩ ብሄሮችና ከ700 የሚበልጡ ቋንቋዎችን ያጠቃልላል።

የብሪታንያ መንግስት በአውስትራሊያ ቅኝ ግዛቱን ሲያቋቁም ከአቦሪጂናል ሕዝቦች ጋር ምንም ዓይነት ውል አልገባም። የብሪታንያ ባለስልጣናት መሬቱን ለመያዝ ሕጋዊ መብት እነደነበራቸው ያምናሉ።

የአቦሪጂናልና የቶሬስ ባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች የራሳቸው ምጣኔ ሐብት እና ጥንታዊና ቀጣይነት የነበረው ከመሬቱ ጋር የተያያዘ ትስስር ነበራቸው። የራሳቸው የሆነ የቆየ የመተዳደሪያ ደንብ የኖራቸው ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን የአዲስ መጪዎችን ህግ ለመቀበል ተገደዋል። አዲስ መጪዎቹ እንዲመጡ አልተጋበዙም፤ እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎም የተቀነላቸው ኣልነበረም።

የአቦሪጂናልና የቶሬስ ባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ኑሮ ሁኔታ በብሪታንያ ቅኝ ገዢዎች መምጣት ምክንያት በመሰረታዊ መልኩ ተለወጠ። ቅኝ ገዢዎች በሚፈጥሩት አዲስ ማሕበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ሐይማኖታዊ ድንጋጌዎች ብዙ ሕይወት አልፏል መሬትም ተወስዷል። ቀድሞ ያልነበሩ እንስሳት፣ እፀዋት እና በሽታዎችም ተከሰቱ።

የቀድሞ አገረ ገዥዎችየብሪታንያ ሰፋሪዎች የአቦሪጂናል ማሕበረሰብን እንዳይጎዱ ቢነግሩአቸውም የብሪቲሽ ሰፋሪዎች ግን የአቦሪጂናል መሬት ለመያዝ ሲሉ ብዙ ሰዎችን ገደሉ። ሰፋሪዎች ለፈፀሙት ግፍ ተገቢ ቅጣት አልተቀጡም።

የተወሠኑ የአቦሪጂናል ማሕበረሰብ ክፍል እና ከአውሮፓ ሰፋሪዎች በሠላም አብረው ይኖሩ ነበር። ኣንዳንድ ሰፋሪዎች የኣቦሪጅን ሰዎችን የከብትና የበግ ጠባቂ ኣድርገው ቀጥረዋቸው ነበር። ኣገረ ገዢው ማኳሪ ኣቦሪጅኖቹን ለእርሻ የሚሆን የየራሳቸው መሬት ሰጥተው ለልጆቻቸውም ትምህርት ቤት ከፍተውላቸዋል። ነገር ግን በጣም ጥቂት የኣቦርጂን ሰዎች ብቻ ናቸው እንደ ሰፋሪዎቹ ለመኖር የፈለጉት እንጂ ብዙዎቹ ባህላቸውና ልምዳቸው እንዲጠፋባቸው ስላልፈለጉ ኣልቀጠሉበትም።

ብዙ ኣቦሪጅኖች ለመሬታቸው ሲሉ ሲዋጉ ተገድለዋል። ቁጥሩ በትክክል እንኳን ባይታወቅም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኣቦሪጂኖች ተገደሉ። በጦርነቱ ከተገደሉትም በላይ ኣውሮፕያውያኑ ባመጡት በሽታ ምክንያት ኣለቁ። የኣቦሪጅኖቹ እልቂት ትልቅ መቅሰፍት ነበር።

# ታሪካዊ ምዕራፍ

## የኣገር ውስጥ ኣሰሳ

በኒው ሳውዝ ዌልስ የመጀመሪያዎቹ ቅኝ ገዢዎች ከፍተኛ ፈተና ኣጋጥሟቸው ነበር። ኣቦሪጅኖችና የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች በደረቁ ምህዳር ላይ መኖር የለመዱት ቢሆንም በድርቅ ጊዜ እነሱም ቢሆን በጣም ይሰቃዩ ነበር።

ሰማያዊ ተራራ /Blue Mountains/ ከሲድኒ ወደ ምዕራብ 50 ኪ/ሜ ርቆ የሚገኘው ተራራ ለሲድኒ ቀደምት ያገር ውስጥ ኣሳሾች ከፍተኛ ፈተና ሆኖ ነበር። በ1813 ሶስት ሰዎች ግሪጎሪ ብላክስ ላንድ፣ ዊልያም ቻርለስ ዌንትወርዝና ዊልያም ላውሰን የሚባሉ ኣሳሾች በመጨረሻ ማቋረጥ ቻሉ። ዛሬ ብሉ ማውንቴንን ኣቋርጦ የተሰራው መንገድና ባቡር እነሱ በቀየሱት መንገድ ነው የሚሄደው።

ከተራራው ባሻገር ኣሳሾቹ ለከብትና ለበግ እርባታ ምቹ የሆነ ሰፊ ቦታ ኣግኝተዋል። ወደ መሃል በገቡ ቁጥር መሬቱ እየደረቀና በረሃማ እየሆነ ይሄዳል።

የኣውሮፓ ኣሳሾች ውሃና በቂ ምግብ መሸከም ላይ ከባድ ችግር ስላጋጠማቸው የመኖር እድላቸው ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ነበር። የጀርመን ተወላጅ የሆኑ ሉድዊግ ሌቻርድ /Ludwig Leichhardt/ የሚባሉ ኣሳሽ በ1848ዓ/ም ሃገሪቱን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ለማቋረጥ ሲሞክሩ ጠፍተዋል።

በ1860 ሮበርት ኦ ሃራ በርክ /O’Hara Burke/ እና ዊልያም ጆን ዊልስ /William John Wills/ ከሜልበርን ተነስተው ከደቡብ ወደ ሰሜን ለማቋረጥ ጀመሩ። ትልቅ ጉዞ ነበር የመሩት ነገር ግን የማቋረጡ ተግባር በጣም ከባድ ነበር። በርክ እና ዊል ብዙ በጫካ የመኖር ልምድ ኣልነበራቸውም። ከኣቦሪጅን የያንድሩዋንዳ ህዝብ የባለሞያ ድጋፍ ያገኙ ቢሆንም ኣሳሾቹ ሲመለሱ መንገድ ላይ ሞተዋል። ምንም እንኳን እነዚህ ኣሳሾች ጉዟቸውን ባይጨርሱም ታሪካቸው በስነጥበብና በስነፅሁፍ እየታወሰ ይኖራል። ይህም የመሬታችን ኣስከፊነት የፈጠረው ኣሳዛኝ ታሪክ ምሳሌ ነው።



## ስፋሪዎችና መስራቾች

ምንም እንኳን በወቅቱ ጥሩ መሬት የነበረ ቢሆንም የሰፋሪዎች ኑሮ በጣም ከባድ ነበር፡፡ ከጎርፍና ከድርቅ በኋላ ሰፋሪዎች መተዳደሪያቸው ሙሉ በሙሉ እየወደመባቸው ስለነበር ገበሬዎቹ ኑሯቸውን እንደ ኣዲስ መጀመር ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ እንደዚህ እያሉ እንደገና በትግል ሲነሱ ቆይተዋል፡፡ የኣውስትራሊያ ታጋዮች /‘Aussie battler’/ የሚለው ኣባባልም የኣውስትራሊያውያን የትግልና ችግርን የመቋቋም መንፈስ የሚገልፅ ነው፡፡ መስራቾቹ በዚህ ጊዜ ላሳለፉት ከባድ ጊዜ ይከበራሉ፡፡ ወንዶች ርቀው ሲሄዱ ወይም ሲሞቱ ሴቶቹ ብዙ ጊዜ የንግድ ወይም የግብርና ስራውን ይሰሩ ነበር፡፡

በዚህ ቀደም ብሎ የነበረው ኣስቸጋሪ ዘመን ነው ኣብዛኛው የኣውስትራሊያ የጓደኝት መንፈስ የዳበረው፡፡ በተለይም ወደ በረሃው የሚሄዱ፣ የበግ ፀጉር የሚላጩና የከብት መንጋ ወደ ገበያ መንዳት ኣብዛኛው የወንዶች ስራ ነበር፡፡ ሰፋሪዎች በችግር ጊዜያቸው እርስ በርስ ይረዳዱ ነበር፡፡ ይህ ልምድ በኣውስትራሊያ የለት ተለት ህይወት የሚንፀባርቅ ነገር ነው፡፡

## የወርቁ ዘመን ጥድፊያ

በ1851 በጀመሪያ በኒው ሳውዝ ዌልስ ኣካባቢ ኣዲስ የወርቅ መኣድን ማውጫ ቦታ መገኘቱ “ሃገሪቷን የሚቀይር ትልቅ ግኝት ነበር፡፡ ከወርቁ መገኘት በኋላ ወዲያው ነው ኣዲሷ የቪክቶሪያ ቅኝ ግዛት ነፃነቷን ያገኘችው፡፡


በ1852 መጀመሪያ ብቻ ወደ 90,000 ሰዎች ከኣውስትራሊያና ከመላው ዓለም ወደ ቪክቶሪያ ጎረፉ፡፡

የዩሬካ ዓመፅ በኣውስትራሊያ የዲሞክራሲ ታሪክ በትልቅነቱ ይታወሳል፡፡ የመንግስት ወታደሮች በወርቅ ቆፋሪዎች ፈቃድ ክፍያ በሚያስከፍሉበት በጣም ያስቸግርሩ ነበር፡፡ በህዳር 11 ቀን 1854, ወደ 10,000 ሰዎች ቤከርይ ሂል፣ ባላራት፣ ተሰብስበው ስለ ከፍተኛ የወርቅ መቆፈሪያ ፈቃድ መነሳት፣ ወደ ቪክቶሪያ ፓርላማ ተወካያቸውን ስለመምረጥና የመሳሰሉ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብቶች ሰነድ ለማፅደቅ ተነሱ፡፡

ይሄንን ተከትሎ የዩሬካ ምሽግ በቁፋሮው ስፍራ ተገነባ። በዚህ ጊዜ ነው ቆፋሪዎቹ (የደቡባዊ የኮከብ መስቀል ኣርማ) ያለው የዓመፅ ባንዲራ ኣዘጋጅተው ሁሉም ቆፋሪዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለመብታቸውና ለነፃነታቸው እንዲታገሉ የተማማሉት። ታህሳስ 3 ቀን 1854 ዓ/ም ጧት ላይ የመንግስት ባለስልጣናት ምሽጉን ለማጥቃት ወታደኦቻቸውን ላኩ። ከኣጭር ውጊያ በኋላ የወርቅ ቆፋርዎች ተሸነፉ ወደ 30 ሰውም ሞተባቸው።

የዓመፁ መሪዎች ተይዘው ወደ ፍርድ ቀረቡ ነገር ግን ችሎቱ ኣልፈረደባቸውም። ንጉሳዊ ኮሚሽኑ መንግስት ጥፋተኛ መሆኑን ተቀበለ የመኣድን ኣውጭዎችም ያቀረቡት የፖለቲካ ውክልና ጨምሮ ኣብዛኛው ጥያቄኣቸው ተመለሰላቸው በዚሁ ዓመት ፒተር ላሎር የተባለው የኣመፁ መሪ የቪክቶሪያ የፓርላማ ኣባል ሆነ።

ከዓመታት በኃላ የዩሬካ ዓመፅ ለፍትሃዊነት የተቃውሞና የእምነት ተምሳሌት ሆነ።


የዩሬካ ባንዴራ/Eureka flag

የወርቅ ጥድፊያው /gold rush/ ኣውስትራሊያን በብዙ መልኩ ቀየራት። በወርቅ ጥድፊያው /gold rush/ ዘመን የኣውስትራሊያ ተወላጅ ያልሆኑ ሰዎች በ1851 ዓ/ም 430,000 የነበረው ቁጥር በ1871 ዓ/ም ወደ 1.7 ሚልዮን ኣሻቀበ። የመጀመሪያው የባቡር ሃዲድና ቴሌግራፍም እያደገ የመጣውን የህዝብ ብዛት ለማሳደግ ሲባል በ1850ዎቹ ተሰሩ።

ከደቡብ አውስትራሊያ በስተቀር በሁሉም ቅኝ ግዛቶች ትልቅ የወርቅ ክምችት ተገኘ። ምጣኔ ሀብቱ አደገ ወርቅም የበግ ሱፍን አልፎት ሄዶ የአውስትራሊያ ዋናው የውጭ ገበያ ምርት ሆነ። በ1890 አካባቢ አውስትራሊያ በዓለም በጣም ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ሀገራት አንዷ ሆነች።

## ሕገወጥ የመሬት ወረራ እና ገበሬዎች

በመጀመሪያው የቅኝ ግዛት ጊዜያት ሕገወጥ የመሬት ወራሪዎች ተብለው የሚጠሩቱ ሰፊ መሬት ወስደው ወደ እርሻ መሬትነት ለወጡት። ምንም እንኳን ለዚህ መሬት ባይከፍሉም ሕገወጥ መሬት ወራሪዎቹ መሬቱ የራሳቸው እንደሆነ ኣሰቡ። ሕገወጥ መሬት ወራሪዎቹ የመጀመሪያውን ጥሩ ምርት ከመሬቱ ካፈሱ በኋላ መንግስት ይሕን መሬት ለማስመለስ ትግል ጀመረ።

በ1860ዎቹ መንግስት በሕገወጥ መሬት ወራሪዎች ተይዞ የነበረውን መሬት ሰራተኛ ወንዶች እና ቤተሰቦቻቸው ለእርሻ እንዲያውሉት ሊሸጥላቸው ፈለገ። ነገር ግን ሕገወጥ የመሬት ወራሪዎቹ የተቻላቸውን ያህል ስፋት ያለው መሬት ለራሳቸው አደረጉ።

የባቡር ሐዲድ መስመር እስከሚዘረጋ ድረስ የእርሻ መሬታቸው ከገበያ የራቀው አዲሶቹ ገበሬዎች ችግር ገጠማቸው። በከተሞች የነበረው ከፍተኛ የስራ ክፍያ መጠን በአንፃሩም በእርሻ ላይ ተሞርኩዞ መኖር እና ከእርሻ የሚገኘው የስራ ክፍያ ዝቅተኛ መሆን የተነሳ የእርሻ ስራ የሚያጓጓ ሊሆን አልቻለም።

የአውስትራሊያው የተሸሻሉ የእርሻ መሳሪያዎች ግኝት የደቡብ አውስትራሊያ እርሻ ስራን ቀላል አደረገው። ለምሳሌ አዲስ በተመነጠሩ የእርሻ መሬት ላይ የሚኖረውን ጉቶ እና ስራስር በቀላሉ አልፎ ማረስ የሚችል የእርሻ መሳሪያ (1870ዎቹ) በቀላሉ ለአዝርዕት እርሻ መጠቀም ኣስቻለ።

## ሰደት በ1800ዎቹ

በ1800 መጀመሪያዎቹ ዋና ዋና የቅኝ ግዛቱ ነዋሪዎች የእንግሊዝ፣ ሰኮቲሽ፣ዌሊሽ እና የታላቋ ብሪታኒያ ተወላጆች ነበሩ። አብዛኛው የአውስትራሊያ ጊዜ ማሳለፊያ፣ ባህላዊ ክንዋኔዎች እና ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የታላቋ ብሪታኒያን ነገር ያንፀባርቁ ነበር። የተወሰኑ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ከአውሮፓ እና ኤሲያ የመጡ ስደተኞችም ነበሩ። በ1800ዎቹ የመጡት አውሮፓዊያን፤ ጣሊያናዊያን፣ ግሪኮች፣ ፖሎች፣ ማልቴስ፣ ሩሳዊያን እንዲሁም በወይን ኢንዱስትሪ የሚሰሩ ፈረንሳዊያን ነበሩ። በአብዛኛው ስራ እና ሀብት ፍለጋ የመጡ ወጣቶች ወይም መርከባቸውን ጥለው የመጡ መርከበኞች ነበሩ።

ከ1842 በኋላ የቻይና ስደተኞች ወደ አውስትራሊያ መምጣት ጀመሩ ወርቅ ከተገኘ በኋላ ደግሞ ቁጥራቸው እያደገ መጣ። የወርቅ ማዕድን ፍለጋ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ላይ ዘር ተኮር ረብሻዎች ነበሩ፤ አንዳንዴም እነዚህ ረብሻዎች ቻይናዊያንን ወደሚቃወም የሕዝብ አመፅ ይቀየራሉ ለምሳሌ በ1854 በቤንዲጎ የተካሄደው ኣንድ ምሳሌ ነው። የእነዚህ ዘር ተኮር ረብሻዎች ውጤትም የመጀመሪያው በ1855 ወደ ቪክቶሪያ እና በ1861ወደ ኒው ሳውዝ ዌልስ ስደትን ማገድ አስከትሏል።

ከ1850ዎቹ የወርቅ መዕድን ግርግር በኋላ ብዙ ቻይናዊያን ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ከቀሩት መካከል በገበያ ተኮር አትክልት እና ፍራፍሬ ስራ ተሰማርተው ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚፈለጉ ትኩስ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለገበያ የሚያቀርቡ ነበሩ።

ከከተማ ራቅ ባሉ የአውስትራሊያ ቦታዎች ላይ የጭነት ግመሎችን የሚያሰማሩ ሰዎች በ1960ዎቹ ከኢራን፣ ግብፅ እና ቱርክ መጡ። ከህንዳዊያኑ ግመል ጠባቂዎች ጋር፤ በአለባበሳቸው እና የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው መመሳሰል ምክንያት በደምሳሳው አፍጋኛውያን ተብለው ይጠሩ ነበር። እነዚህ ግመል ጠባቂዎች ለሀገሪቱ መሃል ምድር ፈር ቀዳጅ ናቸው ተብለው ይቆጠራሉ።

በአነስተኛ ክፍያ እና ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ የሚኖሩ በኲንስላንድ የስኳር እና የሙዝ ኢንዱስትሪ የሚሰሩ ሕንዳዊያን እና የፓሲፊክ ደሴት ዜጎች ነበሩ።

በ1880ዎቹ ከሊባኖስ የመጡ ሠራተኞች ወደ አውስትራሊያ ገቡ። አብዛኛዎቹ በጨርቃ ጨርቅ እና በአልባሳት ኢንዱስትሪዎች የተሰማሩ ሲሆን ብዙ ቁጥር ያላቸው የሊባኖስ ቤተሰቦችም በአውስትራሊያ የሚገኘውን አብዛኛውን የጨርቃ ጨርቅ ንግድ ስራ የግላቸው አድርገውት ነበር።


'አፍጋን /Afghan' የግመል ጎታቾች በበረሃው አውስትራሊያ

## ለአቦሪጂናል የተከለለ ቦታ

በመሬት ይዞታ ላይ በአቦሪጂናል ሕዝቦች እና በሰፋሪዎች መካከል በተደረጉ ቀደምት ጦርነቶች የአቦሪጂናል ሕዝቦች ከማሕበረሰቡ ተገልለው ይኖሩ ነበር። የተወሰኑት ከከተማ በራቁ የበግ እና የዳልጋ ከብት ጣቢያዎች በአብዛኛው ጊዜ ባይከፈላቸውም በዝቅተኛ ዋጋ ተቀጥረው ይሰሩ ነበር። የቅኝ ግዛቱ መንግስታት አቦሪጂናል ሕዝቦች የሚኖሩበትን ቦታ ይከልሉ ነበር ቢሆንም ግን እነዚህ ቦታዎች ኣቦሪጂኖቹ በለመዱት ባሕላዊ አኗኗር ለመኖር የተመቹ አልነበሩም። ለምሳሌ እንደፈለጉ ለማደን እና ለመሰብሰብ አይችሉም ነበር።

በ1800 መጨረሻዎቹ የቅኝ ግዛቱ መንግስታት የአቦሪጂናል እና የባሕረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች መብት በእጃቸው አደረጉ (ወሰዱባቸው)። የ የአቦሪጂናል እና የባሕረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች የት መኖር እንዳለባቸው እና ማንን ማግባት እንደሚችሉ መቆጣጠር ጀመሩ። ብዛት ያላቸው የአቦሪጂናል እና የባሕረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ነጥለው በመውሰድ ለነጭ ቤተሰቦች ወይም ለመንግስት እኀለ ማውታ ማሳደጊያዎች ሰጡአቸው። ይህ ፖሊሲ እስከ 20ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ድረስ በቋሚነት ቀጥሏል። እነዚህ የተሰረቁት ትውልዶች የአቦሪጂናል እና የባሕረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች እና የሌሎች አውስትራሊያዊያን ጥልቅ ሀዘን ምክንያት ሆኖ ቆይቷል በዚህም ምክንያት በ2008 በአውስትራሊያ ምክር ቤት የብሔራዊ እርቅና የይቅርታ ርዕስ ነበር።

## የምርጫ መብት

የምርጫ መብት የሚለው ቃል በመላው ዓለም በምርጫዎች ላይ ለመምረጥ መብታቸው ተጋድሎ የሚያደርጉ ሴቶች የሚጠቀሙበት ስያሜ ነበር። በ1880ዎቹ እና 1890ዎቹ እያንዳንዱ የቅኝ ግዛት ቢያንስ አንድ የመምረጥ መብት የሌለው ማሕበረሰብ ነበራቸው። የመምረጥ መብት የሌላቸው ማሕበረሰቦች ለቅኝ ገዢ ምክር ቤቶች የሚቀርብ በሺ የሚቆጠር የድጋፍ ፊርማ አሰባሰቡ።

በ1895 የደቡብ አውስትራሊያ ሴቶች የመምረጥ መብት እና በምክር ቤት የመመረጥ መብት ተጎናፀፉ። በ1899 የምዕራብ አውስትራሊያ ሴቶች የመምረጥ መብት ተጎናፀፉ።

በ1902 አውስትራሊያ ለሴቶች የመምረጥ እና ለምክር ቤት የመመረጥ መብት የሰጠች የመጀመሪያዋ ሀገር ሆነች። የአቦሪጂናል እና የባሕረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች እስከ 1962 ድረስ የመምረጥ መብት አልተሰጣቸውም ነበር።

በ1923 ኢዲዝ ኮዋን ለምዕራብ አውስትራሊያ ምክር ቤት ስትመረጥ የመጀመሪያዋ ሴት የምክር ቤት አባል ነበረች። በ1943 ኢኒድ ላዮንስ ለአውስትራሊያ ምክር ቤት የተመረጠች የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች።

## ካትሪን ስፔንስ (1825–1910)

ካትሪን ስፔንስ ፀሀፊ፣ ወንጌል ሰባኪ፣ ለሴቶች ጥብቅና የቆሙ እና የሴቶች መብት ተከራካሪ ነበሩ። ከስኮትላንድ ወደ አውስትራሊያ ተሰደው የመማሪያ መፃህፍት እና ሽልማት ያስገኘላቸውን የአውስትራሊያዊያን ኑሮ የተሰኘውን የልብወለድ መፅሀፍት ደርሰዋል።

ቤት አልባ የሆኑትን ሕፃናት የሚረዳ ድርጅት ለማቋቋም እገዛ አደረጉ፤ ለአዲስ መዋዕለ ሕፃናት እና በመንግስት ለተቋቋሙ የሴቶች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እገዛ አደረጉ።

ለምክር ቤት ምርጫ የቀረበች የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች። ምንም እንኳን ብዙ ድምፅ ብታገኝም የምክር ቤት መቀመጫውን አላገኙም። በ1891 በደቡብ አውስትራሊያ የሴቶች መብት ተሟጋች ሊግ ምክትል ፕሬዚዳነት ሆኑ።

ካትሪን ስፔንስ ማድረግ የሚፈለጉ ነገሮችን ማድረግ በማይቻልባቸው ጊዜያት እንኳን ሳይቀር ብርቱ የሆኑ አንድ ሴት መፈፀም ያለባትን ነገር የሚፈፅሙ የጠንካራ ሴት ተምሳሌት ናቸው።



## ፌደሬሽን

ምንም እንኳን ቅኝ ግዛቶቹ በተናጠል የሚመሩ ቢሆንም በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻዎቹ ላይ ብሔራዊ የአኔነት እየጎለበተ መጣ።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻዎቹ አካባቢ ቅኝ ግዛቶችን አንድ ለማድረግ ሁለት ሙከራዎች ተደርገዋል። በ1889 ሰር ሄነሪ ፓርክስ አንድ አዲስ ጠንካራ ሀገር ለመመስረት ጥሪ አቀረቡ። የአውስትራሊያ የፌደራሽን ሃሳብ በተመለከተ በ1890 የአውስትራሊያ ፌደራሽን ስብሰባ ተካሄደ።

የፌደሬሽን እንቅስቃሴዎች ከጥቂት ዓመታት መጓተቶች በኋላ በ1893 መፋጠን ጀመረ። መራጮች የቀጣዩ የህገመንግስቱ ተሰብሳቢ አባላቶቻቸውን መረጡ። መራጮች አዲሱን የአውስትራሊያ ሕገመንግስት ለመቀበል በሁለት ዙር የሕዝበ-ውሳኔ ድምፅ ሰጡ።

የብሪታንያ መንግስት አውስትራሊያ ራስዋን ማስተዳደር እንደምትችል ፈቀደ። በኒው ሳውዝ ዌልስ የፌደሬሽኑን እንቅስቃሴ ይመሩ የነበሩት ኢድሙንድ ባርቶን በጥር ወር 1901 የመጀመሪያው የአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ። መንግስታቸው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በሲድኒ ሰንተኒያል የመዝናኛ ቦታ ቃለ-መሃላ ፈፀሙ።

አሁን አውስትራሊያ በብሪታንያ ግዛት ስር የምትገኝ አገር ሆነች። በመከላከያ እና በውጭ ጉዳይ ላይ እስከ 1931 ድረስ ሙሉ ስልጣን አላገኘችም ነበር። እስከ 1948ቱ የአውስትራሊያ ዜግነት ሕገ ደንብ ድረስ አውስትራሊያዊያን ከአውስትራሊያ ዜግነት ይልቅ በብሪታንያ ጥገኝነት ስር ይኖሩ ነበር። ምንም እንኳን ብሔራዊ ስሜት እያደገ ቢመጣም የብሪታንያ የመሆን ስሜት ግን በዚህ ጊዜም ጠንካራ ነበር።



የፌደሬሽን ቀን በብሪዝቤን 1901

### ኢዲዝ ኮዋን/Edith Cowan (1861 – 1932)

ኢዲዝ ኮዋን ለአውስትራሊያ ምክር ቤት የተመረጡ የመጀመሪያዋ ሴት ሲሆኑ በአውስትራሊያው የአምሳ ብር ኖት ላይ ምስላቸው ይታያል።

ኢዲዝ በሴቶች የምርጫ መብት እንቅስቃሴ ስመጥር እና በሕዝባዊ ትምሕርት እና የሕፃናት መብት ዋና ተሟጋች ነበሩ። ኢዲዝ በ1915 የአጥቢያ ዳኛ በ1920 ደግሞ justice of the peace/የሰላም ዳኛ ነበሩ። በ1921 ኢዲዝ በምእራብ አውስትራሊያ ብሔራዊ ፓርቲ አባልነታቸው የሕግ አውጪ ጉባኤ ኣባል ሆነው ተመረጡ።



## የፖለቲካ ፓርቲዎች መፈጠር

በ1880ዎቹ በአውስትራሊያ የሚገኙ ሠራተኞች ጠንካራ የንግድ ማሕበራትን መስርተው ነበር። ምጣኔ ሀብቱ በወረደ ጊዜ እና በድርቅ ምክንያት እነዚህ ማሕበራት በክፍያ እና በስራ ሁኔታዎች ላይ አመፅ አካሄዱ።

እነዚህ ሠራተኞች በ1891 ሌበር ፓርቲ የተሰኘ የፖለቲካ ፓርቲ ፈጠሩ። የዚህ ዋና ትኩረትም የሰራተኞች ክፍያ እና የስራ ሁኔታ ማሻሻል ነበረ። መካከለኛው መደብ ከሠራተኞቹ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ቢኖረውም ሠራተኞች ያሉበትን ሁኔታ የሚረዳ ነበር። የክፍያ መጠን ለመወሰን እና አመፅን ለማስቀረት ሲባል የመንግስት ቦርድ ተሿሚዎች ነበሩ። የሕብረቱ እርቅ እና ሽምግልና ፍርድ ቤት ሠራተኛው ከባለቤቱ እና ከሶስት ልጆቹ ጋር ቀላል ያለ አኗኗር መኖር የሚያስችለው ዝቅተኛውን የስራ ክፍያ በ1907 ወሰነ።

በ1910 የመጀመሪያው ለዘብተኛ ፓርቲ ተመሰረተ። ይህ ፓርቲ ብሔራዊ ፓርቲ እና የተባበሩት አውስትራሊያ ፓርቲን ጨምሮ ለዓመታት የተለያዩ ስሞች ነበሩት። አሁን የምናውቀው ለዘብተኛ ፓርቲ የተመሰረተው ሮበርት መንዚስ በተባሉ አውስትራሊያን ለረጅም ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገለገሉ ግለሰብ በ1944 ነው።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የገበሬዎችን ተጋድሎ ከፍ ለማድረግ የገጠር ፓርቲ /Country Party/ ተመሰረተ። በአሁኑ ጊዜ ብሔራዊ ፓርቲ በመባል ይታወቃል ከለዘብተኛው ፓርቲም ጋር በጥምረት ይሰራል።

## የ1901 የስደት ገደብ ውሳኔ

የስደት ገደብ ውሳኔ በታህሳስ 1901 ሲፀድቅ የነጮች አውስትራሊያ ፖሊሲ ሕግ ሆነ። ስደተኞች በአውስትራሊያ መስራት እንዳይችሉ እንዲሁም ነጭ ያልሆኑ ሰዎች በስደተኝነት እንዳይመጡ አገደ።

ከአውሮፓዊያን ውጭ የሆኑ ሰዎች 50 ለሚደረሱ ቃላት በአውሮፓ ቋንቋ ለቃለ-መጠይቅ እንዲቀመጡ ተደረገ። የቻይናው የንግድ ምክር ቤት አባል የሆኑት የሕግ ጠበቃው ዊልያም አህ ኬት እና የታወቁ ቻይናዊ ነጋዴ የህዝብ አመፅ አስነሱ፤ ቢሆንም ግን ይህ ሕጉን ለማስቀየር አልረዳቸውም።

በአዲሲቷ የተባበረችው አውስትራሊያ የአውሮፓ ስደተኞች ስመጥር ነበሩ። ሆኖም ግን ቻይናዊያን፣ ሕንዳዊያን፣ ከፓሲፊክ ደሴት እና ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡ ሕዝቦች የአውስትራሊያ ማሕበራዊ ማንነት አካል ነበሩ።

### ዶሮቴ ማኬላ (1885–1968)

ዶሮቴ ማኬላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1908 የታተመው *ሐገሬ በሚለው* ግጥም በጣም ታዋቂ የሆኑ ገጣሚ ሲሆኑ «ፀሐይ ያቃጠላት ሀገር» በሚለው ስራቸው ለዘለዓለም ሲታወሱ ይኖራሉ። የእሳቸው ስነ-ግጥም በሰሜናዊ ምዕራብ አውስትራሊያ በጋንዳህ አጠገብ በሚገኘው የወንድማቸው እርሻ ላይ ያላቸውን የመልካም አርአያ የጫካ ስነ ግጥም ግምት ውስጥ ያስገባ ተደርጎ ይታያል።

ዶሮቴ ለአውስትራሊያ ስነፅሁፍ ባበረከቱት አስተዋፅዖ መሰረት በብሪቲሽ ግዛት በ1968 ከፍተኛ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።



## የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት (1914–18)

በአቦሪጂናል እና በሰፋሪዎች መካከል ከነበረው ግጭት በስተቀር አውስትራሊያ የሚደነቅ ሠላማዊ የሆነ ታሪክ ነበራት። የእርስበርስ ጦርነት ወይም ስርነቀል ለውጥ አልታየም።

የአውስትራሊያ ትውልዶች ለብሪታንያ ግዛት በጣም ታማኝ ሆነው ቆይተዋል።

የአውሮፓውያን የጦር ሰፈር ለኤስያ ከመቅረቡ የተነሳ አውስትራሊያ በታሪክ ለጥቃት የተጋላጭነት ስሜት ያላት ሆና ቆይታለች በተለይም ከጃፓን ፈርጣማ ኃያል ኣንፃር። የብሪታንያ መንግስትና ባሕር ኃይሏ ጥንካሬ አውስትራሊያን እንደሚከላከልልን ተማመንን። ኣውስትራሊያ ለብሪቲሽ ግዛት ጥንካሬ እና ብሪታንያ አውስትራሊያን እንድትከላከልላት በማለት በሁለቱም የዓለም ጦርነቶች ላይ ከብሪታንያ ጋር ኣብራ ተዋግታለች።

አውስትራሊያ በነሐሴ 1914 የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ገባች በ1915 ደግሞ በጀርመን ቱርክ ኅብረት ማጥቃት ላይ ተሳትፋለች። የአውስትራሊያ እና ኒው ዚላንድ ወታደራዊ ኮሮች (አንዛክስ) ሰዎች በውሃ የተከበበችውን የጋሊፖሊ መሬት ለማጥቃት ሃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር።

ከቱርክ ወታደሮች ተኩስ ለመግጠም ቀጥ ያለውን ገደል መውጣት ነበረባቸው። እንደምንም ገደሉን ወጥተው ምሽግ ቆፈሩ ብዙ ወጣት ወንዶች ቢሞቱም። አውስትራሊያዊያን በአንዛክስ ወኔ ትልቅ ኩራት ይዘው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል።

ከጋሊፖሊ በኋላ የአውስትራሊያ የጦር ሀይሎች በምዕራብ ግንባር በፈረንሳይ እና ቤልጂየም ተዋግተዋል። 'ቆፋሪዎች' የሚለውን ስም ያገኙት እዚህ ነበር ምክንያቱም ብዙ ጊዜአቸውን ያጠፉት ምሽግ በመቆፈር እና በማበጀት ነው። ለፈረንሳይ ወዳጅነት ምስጋና ይግባውና በእነሱ አጋዥነት እና በዋና አዛዣቸው መቶ አለቃ ሰር ጆን ሞናሽ የሚመራ የአውስትራሊያው ቆፋሪዎች በመጨረሻዎቹ ጦርነቶች ጀርመንን በመውጋት ትልቅ ድል ተጎናፀፈ።

የውትድርና አገልግሎት የሚሰጡ ወንድ እና ሴት አውስትራሊያዊያን በመካከለኛው ምስራቅ የስዊዝ ካናል በመከላከል ላይም ተሳትፈዋል፤የሲናይ ባሕር-ገብ እና በፍልስጤምም እንደዚሁ።

## ሲምሰን እና አህያው —ጆን ሲምሰን ኪርክፓትሪክ(1892–1915)

ተራ ወታደሩ ጆን ሲምሰን በጋሊፖሊ ወታደራዊ የሕክምና ጓድ ቃሬዛ ተሸካሚ በመሆን አገልግሏል። ቃሬዛ ተሸክሞ በጉብታ እና ሸለቆ ቦታዎች መጓዝ አስቸጋሪ ነበር። ከወታደራዊ ትእዛዝ አንፃር ዳፍይ ተብሎ የሚጠራ አህያ የቆሰሉ ወታደሮችን ወደ ሰላማዊ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቀም ነበር።

ቀን እና ማታ በየሠዓቱ ሲምሰን እና አህያው ለሕይወታቸው ሳይሳሱ በውጊያዎች መካከል እና በባሕር ዳርቻ ላይ በሚገኘው የጦር ሰፈር ይመላለሱ ነበር።

ተራ ወታደር ጆን ሲምሰን በሚያዝያ 25 1915 ጋሊፖሊ ደረሰ። ልክ ከአራት ሳምንታት በኋላ በጠላት ጠመንጃ ተገደለ። የውትድርና አገልግሎት የሚሰጡ ወንዶች በባሕር ዳርቻው በሚገኘው ጦር ሰፈር ሆነው ዳፍይ ወጣት አለቃውን ከጎኑ ሳያደርግ አሁንም የቆሰሉ ወታደሮችን ተሸክሞ ወደ ባሕር ዳርቻው ሲያሻግር በሃዘን እና በትካዜ ይመለከቱት ነበር። ጆን ሲምሰን ኪርክፓትሪክ ዝነኛ አውስትራሊያዊ ነው።





# የአንዛክ ዝና

የአንዛክ ልምድ በቱርኳ ጋሊፖሊ የባሕር ወሽመጥ ቀስ በቀስ ተሸጋገረ።

የሚያዝያ 25 ቀን 1915ቱ ጋሊፖሊ መግባት 8 ወር የፈጀ ዘመቻ ያስከተለ ሲሆን ከዚህም ተያይዞ ከ8000 በላይ የተገደሉ ወይም በበሽታ የሞቱትን ጨምሮ ከ26,000 የሚበልጡ አውስትራሊያዊያን ጉዳት ደርሶባቸዋል። በጋሊፖሊ የባሕር ወሽመጥ ያገለገሉ ወታደሮች ጀግንነት፣ ወኔ ና ዝናን አተረፉ አንዛክ የሚለውም ስም የአውስትራሊያ እና የኒው ዚላንድ ቋንቋ ሆነ።

በሚያዝያ 25 1916 አውስትራሊያ፣ ኒው ዚላንድ፣ ኢንግላንድ እና በግብፅ የሚገኙ ወታደሮች እዚያ የገቡበት የመጀመሪያውን በዓል አከበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሚያዝያ 25 የአንዛክ ቀን በመባል የታወቃል።

በ1920ዎቹ የአንዛክ ቀን ክብረ-በዓል በመላው አውስትራሊያ ይከበር ነበር መንግስትም የአንዛክ ቀን ሕዝባዊ በዓል አድርጎ ሰየመው።

ዋና ዋና የጦርነቱ መታሰቢያዎች በዋና ከተሞች፤ ሀወልት ደግሞ በሀገሪቱ በሚገኙ ትልልቅ እና ትናንሽ ከተሞች የተገነቡት ምክንያት በጦርነት እና ኋላ በነበሩ ግጭቶች ሕይወታቸውን ላጡ ወጣት ወንድ እና ሴት ምስጋና ለማቅረብ ነው።

የአንዛክ ቀን ማለት በጦርነት፣ ግጭቶች እና ሰላም ማስከበር ስራዎች ለተሳተፉ ጀግኖች ክብር፣ በእኩል ዓይን እይታቸው፣ የወደፊቱ ተስፋችን እንዲለመልም በመከራ እና መስዋትነት ፊት የነበራቸው ፅናት የሚገለፅበት ቀን ነው። ብዙ የተለያዩ የጦርነት ትርጉም የሚንፀባረቅበት ቀን ነው።

ዛሬ የአንዛክ ቀን በአውስትራሊያ እና በመላው ዓለም ታስቦ ይውላል። የውትድርና አገልግሎታቸውን የጨረሱ ወንድ እና ሴት፣ የሠላም አስከባሪ እና ከሌሎች ሀገሮች ከዘመቻ የተመለሱ ጀግኖች ሁሉም የአንዛክ ቀንን በኩራት እና በአድናቆት በሰልፍ ትርዒት ያከብራሉ።

## የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል (1929–32)

የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል ለአውስትራሊያ ሕዝብ ክፉ ቀን ነበር። የኒው ዮርክ የገበያ ምንዛሪ በወደቀበት በጥቅምት 1929 በተመሳሳይ ጊዜ ጀመረ። የአውስትራሊያ ሽቀጥ መውደቅ፣ ቀጣሪዎች ስራና ክፍያ በመቀነሳቸው የተፈጠረ የኢንዱስትሪ አብዮት ለአውስትራሊያ የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል ሌሎች ምክንያቶች ነበሩ። በ1932 አጋማሽ ወደ 32 በመቶ የሚጠጉ አውስትራሊያዊያን ከሥራ ውጭ ነበሩ።

የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆሉ ተፅእኖ በአውስትራሊያ ማሕበረሰብ ዘንድ አስደንጋጭ ነበረ። ከሥራ ውጭ በመሆን እና ለውጥ በሌለው ገቢ ምክንያት ብዙ ሰዎች ቤታቸውን አጡ። ያለ ማሞቂያ ወይም ንፅሕና በጊዜያዊ መጠለያ ለመኖር ተገደዱ። አንዳንድ አባቶች ያለ ምንም እገዛ ቤተሰባቸውን ጥለው ጠፉ ወይም ጠጪዎች ሆኑ። ብዙ የሠራተኛው መደብ ልጆች በ13 ወይም 14 ዓመታቸው ትምህርታቸውን አቋረጡ። ብዙ ሴቶች በአነስተኛ ስራዎች ላይ ተሰማሩ ልጆቻቸውን እና ቤታቸውን በራሳቸው መጠበቅ ጀመሩ።

በጊዜው እስከ የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል ክስተት ድረስ መንግስት ማዕከላዊ የስራ አጥ ማዕቀፍ አልነበረውም። ከእርዳታ ሰጪ እና የተወሰኑ የግል ድርጅቶች ውጭ ድሃው ሕዝብ በመንግስት ስራዎች እና የቅጥር ፕሮጀክቶች መተማመን ነበረበት። ምጣኔ ሃብቱ በ1932 ማንሰራራት ጀመረ ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች የቤተሰቦች ጉዳት ግን ማገገም አልቻለም።

በምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆሉ ጊዜ ዋናዎቹ የአውስትራሊያ ግብረሰናይ ድርጅቶች እና ወዶ-ዘማች ድርሻ ጎላ ብሎ ይታይ ነበር።



የክፉ ዘመኑ የዶሮ ሾርባ

## ሰር ቻርለስ ኪንግስፎርድ ስሚዝ (1897–1935)

ሰር ቻርለስ ኪንግስፎርድ ስሚዝ ቀደም ሲል የአውስትራሊያ አብራሪ ነበሩ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት በጋሊፖሊ ተዋግተዋል፤ ከብሪታኒያው አየር ወለድ ጋርም በረዋል።

ትልቁ ያከናወኗቸው ነገር ቢኖር በ1928 ከካሊፎርኒያ ተነስተው የፓሲፊክ ውቂያኖስን አቋርጠው ኩዊንስላንድ የደረሱ የመጀመሪያ ሰው መሆናቸው ነበር። ደቡባዊ መስቀል /Southern Cross/ ተብላ የተሰየመችው የሚያበሯትን አውሮፕላን ይዘው ኣውስትራሊያ ሲደርሱ 25,000 አድናቂዎቻቸው ለጀግናቸው ‘ስሚዝይ’ እያሉ ደስታቸውን ይገልፁ ነበር። ለበረራ አገልግሎታቸው በ1932 የጀግና መዓረግ ተሰጣቸው።

በ1935 ከኢንግላንድ ወደ አውስትራሊያ በሚበሩበት ጊዜ በአሳዛኝ ሁኔታ አውሮፕላኑ ተከሰከሰ በጭራሽ ማግኘትም አልተቻለም።

ሰር ቻርለስ ኪንግፎርድ ስሚዝ የዓለም ድንቅ አብራሪ ተብለው ተሰይመዋል። በምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል መሃል የመጣ እውነተኛ የሚከበር እና የሚደነቅ የአውስትራሊያ ጀግና ሆነው ሲታወሱ ይኖራሉ።



## ሁለተኛው የዓለም ጦርነት (1939–45)

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አውስትራሊያ የጀርመን ተቃራኒ ሆና በአውሮፓ፣ ሜዲትራኒያን እና ሰሜን አፍሪካ ከተባበሩት ጋር ተዋግታለች። በደቡብ ምስራቅ ኤስያ እና በፓሲፊክ ደግሞ ከጃፓን ጋር ተዋግተዋል።

በሰሜን አፍሪካው ምድረ በዳ በመጨረሻው ጀርመኖች በግብፅ እየገፉ የመጡትን የመከላከል ውጊያ በቶብሩክ ከተማ የነበረው ረጅሙን የጀርመን እና የጣሊያን ከበባ የአውስትራሊያ ወታደሮች ተቋቁመውታል። (አብዛኞቹ የአውስትራሊያ) የሆኑ እነዚህ ሰዎች የከረረ ጥቃት እና ከባድ ሁኔታን ለስምንት ወራት ያህል በዋሻ እና ሽንተረር እየኖሩ ተቋቁመውታል። ውሳኔአቸው፣ ጀግንነት እና የቀልድ ለዛቸው ከሰፊ የአለቆቻቸው ዕቅድ ጋር ተዳምሮ በጦርነቱ ያጋጥሙ የነበሩትን አንዳንድ ክፉ ቀናት በመንፈስ ጠንካራነት እንዲያልፉት ኣድርጓቸዋል። ‘እንዲህ በማድረግ ረዘም ላለ ጊዜ’የቶብሩክ አይጥ’ የሚል ዝና አግኝተዋል።

በ1941 ጃፓን በፓሲፊክ ጦርነት አወጀች። የውትድርና አገልግሎት ለመስጠት የተመለመሉ የአውስትራሊያ ወንድ እና ሴቶች ፓፓዋ ኒው ጊኒን ለመከላከል ተሰማሩ። ይህ ስራ ለመደበኛ ወታደሮች እና በደንብ ላልሰለጠኑ ወጣት የሆኑ የግዴታ ምልምል ወታደር ተላልፎ ተሰጥቶ ነበር። ጥቅጥቅ ባለው ደን፣ ዥው ያለ ገደል፣ የኮኮዳ ጉዞ ተብሎ የሚጠራ ጎታች የሆነ ረግረጋማ ቦታዎች ከጠላት ጋር ተዋግተዋል። የአውስትራሊያ ወታደሮች የጃፓን ግስጋሴን አስቆሙት። በጋሊፖሊ እንደ አንዛክ ሰው ኮኮዳ ጉዞም ለአንዳንድ አውስትራሊያዊያን የመንፈሳዊ ጉዞ ያህል ሆኗል።

በ1942 ጃፓኖች በሲንጋፖር የነበረውን የብሪታንያ ወታደራዊ ሰፈር በእጃቸው አስገቡት። ከተማረኩ በኋላ ወደ ታይ-በርማ የባቡር ሐዲድ ስራ ላይ እንዲሰሩ ከተወሰዱት መካከል 15,000 የሚጠጉት የአውስትራሊያ ወታደሮች ነበሩ። በስራው ላይ ብዙ የአውስትራሊያ ወታደሮች በጃፓኖች ጭካኔ የተሞላበት አያያዝ ስር ወድቀው ነበር። ምንም አንኳን አውስትራሊያዊያን የጦር እስረኞች እርስ በርስ ለመጠባበቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ቢያደርጉም 2700 የሚጠጉ አውስትራሊያዊ የጦር እስረኞች የሞቱት በዚሁ ነበር።



በኮኮዳ መንገድ የቆሰለውን ወታደር በፓፓዋ ተንከባባቢ ስለመረዳቱ

## ሰር ኢድዋርድ ዊርይ ዳንሎፕ (1907–93)

ሰር ኢድዋርድ ዊርይ ዳንሎፕ ደፋርና ተንከባካቢ የቀዶ ጥገና ሐኪም እና የአውስትራሊያ የጦር ጀግና ነበሩ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በጃፓኖች ተማርከው ለታይ-በርማ የባቡር ሐዲድ ስራ ወደ በርማ ተወሰዱ። ይህ በጣም አድካሚ ሥራ ነበር።

እንደ አዛዥ ዊርይ ስለ ሰዎች በድፍረት ይናገራሉ፣ እንደ ቀዶ ጥገና ሐኪምነታቸው ረጅሙን ሰዓት የሰዎችን ጤንነት በመጠበቅ ያሳልፋሉ። በጦር ሰፈሩ ከባድ ሕመም ቢሰማቸውም ሕመማቸውን ተቋቁመው አገልግሎት ይሰጡ ነበር።

በ1969 በሕክምና ላበረከቱት አስተዋፅኦ የጀግና ማዕረግ ተሰጣቸው። ሲሞቱ ከ10,000 በላይ የሚሆን ሰው በሜልቦርን ጎዳና ላይ ተሰልፎ የጀግናውን የቀብር ስነስርዓት የባቡር ሐዲዱ ቀዶ ጠጋኝ ጀግና ሐኪም’ በማለት ሰዓተ ቀብራቸውን ፈፅሞላቸዋል።



## ሌሎች ግጭቶች

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ወዲያውኑ ከ1950 እስከ 1953 እንደ የተባበሩት መንግስታት ጦር አንዱ አካል ሆኖ ደቡብ ኮሪያን ከኮምኒስቱ ሰሜን ኮሪያ ለመከላከል የአውስትራሊያ የጦር ኃይል ተላከ።

አገሪቱን ለማዋሃድ ከሚፈልገው የቬትናም ኮምኒስት ኃይሎች ደቡብ ቬትናምን ለመከላከል ከአጭር ጊዜ በኋላ አውስትራሊያ አሜሪካንን ተቀላቀለች። ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት ወዲህ የአውስትራሊያ ጦር በሙሉ ቆራጥነት የገባበት ትልቁ ውጊያ በቬትናም የነበረው ጦርነት ነው። ከ1962 እስከ 1973 በአውስትራሊያ ታሪክ ሃገሪቱ የተዋጋችበት ረጅሙ የጦርነት ጊዜ ይሄ ነው። ኣወዛጋቢ የጦርነት ተሳትፎ በመኖሩ ምክንያት ብዙ የአውስትራሊያ ዜጎች ለተቃውሞ ሰልፍ ኣስወጥቷል። በተለይም ወጣት ኣውስትራሊያውያን በግዴታ እየተመለመሉ ወደ ጦርነት መማገዱ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ ነበር።

የአውስትራሊያ የጦር ኃይል በምስራቅ ቲሞር፣ ኢራቅ፣ ሱዳን እና አፍጋኒሰታን ግጭቶች ላይ ተሳትፎ ነበር። አፍሪካ፣ መካከለኛው ምስራቅ እና ኤስያ-ፓሲፊክን ጨምሮ በተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪነትም ተሳትፈዋል።

## የመታሰቢያ ቀን

ከአንዛክ በተጨማሪ አገልግሎት ለሰጡ እና በጦርነት ለሞቱ አውስትራሊያዊያን መታሰቢያ ቀን ይደረግላቸዋል። አውስትራሊያዊያን ሕዳር 11 (11ኛው ወር) ከጧቱ 05:00 ሰዓት በየዓመቱ በጦርነት እና ግጭት ለተጎዱ፣ ሕይወታቸውን ላጡ እንዲሁም አገልግሎት ለሰጡ ወንድ እና ሴት ለማስታወስ የህሊና ፀሎት ይደረግላቸዋል። በዚህ ቀን ቀይ አበባ እናደርጋለን።

# ሰደት በ1900ዎቹ መጀመሪያ

በአንደኛው እና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች መካከል የነበረው ወደ አውስትራሊያ የመግባቱ ክልከላ እንዳለ ቀጠለ። ቢሆንም ግን የስደተኞች ቁጥር ጨመረ በተለይም ከደቡብ አውሮፓ የሚመጡ ወንዶች። ብዙ ችሎታ፣ እውቀት እና የራሳቸው የግላቸው የሆኑ ባህላዊ እሴቶች ይዘው መጡ። ለአውስትራሊያ የገጠር ኢንዱሰትሪ እድገት እገዛ አደረጉ፣ መንገድ እና የባቡር ሐዲድም ሰሩ። የሰለጠኑ ጣሊያናዊያን ድንጋይ ጠራቢዎች የመንግስት ሕንፃዎችን እና መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።



ወደ ኣውስትራሊያ የመጡ የኣውሮፓ ስደተኞች

በ1930 መጨረሻዎቹ የእስራኤል ጥገኝነት ጠያቂዎች ከአውሮፓ መምጣት ጀመሩ። ከናዚ ጀርመን ስጋት ለማምለጥ ሲሉ ነበር። ከጀርመን፣ ኦስትሪያ፣ ቺኮዝላቫኪያ፣ ሃንጋሪ እና ፖላንድ መጡ። አብዛኛዎቹ የተማሩ ስለነበሩ ለአውስትራሊያ ምጣኔ ሀብት እና ባህል የማይናቅ አስተዋፅኦ አበረከቱ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተማረኩ ቁጥራቸው 18,000 የሚጠጉ የጣሊያን ምርኮኛ ወታደሮች በአውስትራሊያ የጦር ካምፕ እስርቤት ታስረው ይገኙ ነበር። በካምፑ የሚቆዩት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር የሚቆዩት። በእስር ቤቱ ሲቆዩ ጥሩ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል ብዙዎቹም ስለ ሀገሩ እና ሕዝቡ አንዳንድ ነገሮች አውቀዋል። ከጦርነቱ በኋላ ብዙዎቹ ስደተኛ ሆነው ወደ አውስትራሊያ ተመልሰዋል።

# የድህረ-ጦርነት የጥገኝት ጠያቂዎች

ከጦርነቱ በኋላ የኣውስትርሊያ የህዝብ ቁጥር ለመጨመር ሲባል ከሌሎች የአውሮፓ አገሮችሥደተኞች እንዲመጡ አውስተራሊያ ታበረታታ ነበር። በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ናዚ ጀርመንን ሸሽቶ ሄደ ወይም በአሁኑ ጊዜ በሶቪየት ሩሲያ በመያዝቸው ምክያት ወደ ትውልድ አገራቸው መመለስ አልቻሉም። በግምት 170,000 የሚሆኑ እነዚህ የተፈናቀሉ ሰዎች አውስትራሊያ ተቀብላ አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ ኣድርጋለች።

በአውስትራሊያ ደግሞ ከፍተኛ የሰራተኛ እጥረት ነበር። በዚያን ወቅት የነበረው መንግስት የሕዝብ ቁጥር መጨመር ለወደፊት ለሀገሪቱ አስፈላጊ እንደሆነ እምነት ነበረው። ጤነኛ የሆኑ እና እድሜአቸው ከ 45 ዓመት በታች የሆኑ ስደተኞች በ£10 ልጆቻቸው ደግሞ በነፃ ወደ አውስትራሊያ ይጓዙ ነበር። ይሁን እንጂ ሥደተኞቹ አሁንም ቢሆን የብሪቲሽ ወይም የአውሮፓ ዜግነት ያላቸው ናቸው።



# Snowy Mountains በውሃ ኃይል የሚሰራ የኤሌክትሪክ ማመንጫ

በ1949 መንግስት ወደ ምስራቃዊ ቪክቶሪያ ባሕር ይፈሱ ከነበሩ የበረዶማ ወንዞች ላይ ስፋት ያለው የግድብ ስራ ጀመረ። ለመስኖ እና ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት አገልግሎት ለማዋል ሲባል የዚህ ውሃ ፍሰት ወደ መሃል ሀገር ተቀይሷል። ለማጠናቀቅ 25 ዓመት የፈጀ ስፋት ያለው ፕሮጀክት ነው።

ይህ ትልቁ የአውስትራሊያ የምህንድስና ፕሮጀክት ነው። ከዓለም ትልቁ በውሃ ኃይል የሚሰራ የኤሌክትሪክ ማመንጫ እንዲሁም የዓለም ቁንጮ የሆነ አድናቆት የተቸረው ዘመናዊ የምህንድስና ውጤት ነው።

የበረዶማ ተራራ ስራ በኮሲስኮ ብሔራዊ ፓርክ በኒው ሳውዝ ዌልስ ይገኛል። በውስጡ 16 ዋና ግድቦች፣ ሰባት የኃይል ማመንጫ፣ አንድ የንፊታ ጣቢያ እና 225 ኪሎሜትር ዋሻ፣ የቧንቧ መስመር እና የመጠጥ ውሃ መሄጃ ቦይ ይይዛል። በአብዛኛው በመሬት ስር ነው።

ይህ ስራ በኒው ሳውዝ ዌልስ እና በቪክቶሪያ ለሚገኙ እርሻዎች ዋና የውሃ አቅርቦት ምንጭ ነው። የኃይል ማመንጫዎቹ የኒው ሳውዝ ዌልስ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ10 በመቶ ይሸፍናል።

ስራው በ1949 ተጀምሮ በ1974 ተጠናቀቀ። ቁጥራቸው ከ100,000 በላይ የሆኑ ከ30 አገራት የመጡ ሰዎች በፕሮጀክቱ ስራ ሰርተዋል። ሰባት በመቶ የሚሆኑ እነዚህ ሰራተኞች ስደተኞች ነበሩ። ፕሮጅቸቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አብዛኛው የአውሮፓ ዜግነት ያላቸው ሰራተኞች አውስትራሊያ መኖር ቀጠሉ ለባህል ብዝሃነትም የራሳቸውን ድርሻ አበረከቱ።

የበረዶማ ተራራዎች ስራ ፋይዳ ያለው የአውስተራሊያ ነፃነት፣ የባህል ብዝሀነት እና የሀገር ሀብት የሚገልፅ የማንነት አርማ ነው።

## የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች አቀባበል

በ1940ዎቹ እና 1950ዎቹ በአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች የመንግስት አቋም የውህደት አንዱ አካል ነው። ይህም ማለት የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች መጤ ከሆኑ ማሕበረሰቦች ጋር እኩል መኖር እንዲችሉ ተነገራቸው። ይህ ግን ሊሰራ አልቻለም ምክንያቱም ባህላቸውን ማጣት አልፈለጉም።

በ1960ዎቹ አንድነትን የሚያቀነቅን የመመሪያ ለውጥ ተደረገ። በ1950ዎቹ አብዛኛው የአውስትራሊያ ወንዶች የመምረጥ መብት ተጎናፀፉ ሆኖም ግን የኮመንዌልዝ የመምረጥ መብት እስከ 1962 ድረስ ለሁሉም የአቦሪጊናል ህዝቦች አልተሰጠም ነበር። እንደ የአንድነቱ አካል የአቦሪጂናል ህዝቦች የሰው ልጅ ነፃነት ቢሰጣቸውም ነገር ግን አሁንም የመጤ ባህሉን እንዲላመዱ ይጠበቅባቸው ነበር።

በ1967 ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ አውስትራላዊያን የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች በአውስትራሊያው የአምስት ዓመቱ የህዝብ እና ቤቶች ቆጠራ እንዲካተቱ ታሪካዊ የሕዝብ ውሳኔ አሳለፉ። ይህ እንደሚያሳየው በጊዜው አብዛኛው አውስትራሊያውያን ሀሳብ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች እንደ ማንኛውም ሰው እኩል መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ነው።

ይህ የበለፀገ የማሕበረሰብ እሴት እና የአቦሪጂናል ተቃውሞ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች አስመልክቶ ወደ የራስን ዕድል መወሰን የፖሊሲ መርህ አመራ። የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች በአስተዳደር፣ ምጣኔ ሀብት፣ ማሕበራዊ እና ባህላዊ ልማት የራሳቸው የሆነ ተሰሚነት እንዲኖራቸው ማስፈለጉን መንግስት አመነ።

በ1960ዎቹ የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ አመፅ በዌቭ ኮረብታማው የሰሜኑ ግዛት የጉሪንጂ አመፅ ጋር የሕዝብ ተቀባይነትን አገኘ። በቪንሰንት ሊንጊያሪ የሚመራ የአቦሪጂናል እንስሳት አርቢዎች የክፍያ እና የስራ ሁኔታን አስመልክቶ በእንስሳት እርባታ ጣቢያው ላይ የስራ ማቆም አድማ አደረጉ። የእነሱ ድርጊት ኢዴ ማቦ እና ሌሎች ለመሬት ባለቤትነት መብት ትግል በር ከፈተላቸው።

የ1976ቱ የአቦሪጂናል የመሬት ባለቤትነት መብት (የሰሜናዊው ግዛት) ድንጋጌ መሰረት የአቦሪጂናል ማሕበረሰብ ከከተማ የራቀ የአውስትራሊያ ክፍል ላይ መሬት ተሰጣቸው። 1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የከፍተኛው ፍርድቤት የማቦ ውሳኔ እና *የ1993ቱ የነዋሪነት ድንጋጌ* የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ከመሬት ጋር ተያይዞ የራሳቸውን ባህላዊ ሕግ እና ደንብ መሰረት ያደረገ ጥያቄ እውቅና ይሰጣል።

በአውስትራሊያ መብታቸውን የሚጠይቁ ብዛት እየጨመረ መሄዱ ታየ። በእነዚህ ዙሪያ የባሕላዊ ማሕበረሰብ ዝንባሌ ቀጥሏል።

በግንቦት ወር 1997 እነሱን ወደ ሀገርቤት ማስመጣት የተሰኘ ሪፖርት ለአውስትራሊያ ምክር ቤት ቀርቧል። ሪፖርቱ ብዛት ያለው የአቦሪጂን እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ልጆች የሆኑ ህፃናትን ከቤተሰቦቻቸው ለይቶ የመውሰድ ውጤት ነው። እነዚህ ልጆች የተሰረቁ ዜጋዎች ተብለው እስከመጠራት ደርሰዋል። በሪፖርቱ ምክንያት በሺ የሚቆጠሩ አውስትራሊያዊያን አቻዎቻቸው ለሆኑ ነባር የአውስትራሊያ ዜጎች በ1998 በተደረገው የይቅርታ ቀን በሕብረት ሆነው ድጋፋቸውን ገልፀዋል።

## አገሪቱ ለተሰረቀው ትውልድ ይቅርታ ጠይቃለች (2008)

በ የካቲት ወር 2008 የአውስትራሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር በመላው አውስትራሊያዊያን ስም ለተሰረቁ ዜጎች ብሔራዊ ይቅርታ አስመልክቶ በአውስትራሊያ ምክር ቤት ንግግር አድርጓል። ጠቅላይ ሚኒስተሩ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ቀደም ሲል የተስተናገዱበት አግባብነት ለሌለው የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ልጆች ከወላጆቻቸው ተለይተው የተወሰዱበት መንገድ ይቅርታ ጠየቁ።

ንግግሩ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን ጣቢያዎች ተላልፏል። በሺ የሚቆጠሩ የአውስትራሊያዊያን የይቅርታ ንግግሩን ለማድመጥ በሕብረት በመሰብሰቢያ ቦታዎች እና በስራ ቦታዎቻቸው ላይ ተገኝተዋል። ንግግሩ በዝርዝር አግባብነት በሌለው መንገድ በፈፀሙ ላለፈው ድርጊት በይፋ ይቅርታ ጠይቀዋል። የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ቁስል ለመሻር እና እነዚህ ድርጊቶች ለወደፊቱ እንዳይደገሙ ይህ በጣም ጠቃሚ የሆነ እርምጃ ነው። የይቅርታ ንግግሩ ለሁሉም አውስትራሊያዊያን ጠቃሚ የሆነ የወደፊቱ እርምጃ ነው።በአሁኑ ጊዜ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች እርባና ያለው አስተዋፅኦ ለአውስትራሊያ ማህበረሰብ ማንነት እውቅና የሰጠ እና በስፋት የሚታወስ ነው። ብዙ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች በመላው የአውስትራሊያ ማህበረስብ ውስጥ የፍርድ ቤት፣ አስተዳደር፣ በጥበብ እና ስፖርትን ጨምሮ ከፍተኛ የአመራር እርከኖችን ይዘው ይገኛሉ።



የስካይ ራይተር ፀሃፊዎች 'ሶሪ/Sorry'በሲድኒ ላይ

## አልበርት ናማትጂራ (1902–59)




አልበርት ናማትጂራ የበቁ አውስትራሊያዊ የአዲስ የአሳሳል ዘዴ ፈር ቀዳጅ የጥበብ ሰው ነበሩ። እንደ የአረርንተ ወጣት አልበርት የተፈጥሮ ስጦታቸው የሆነውን የአሳሳል ጥበብ አሳይተዋል። የመደበኛ ትምህርታቸው አነስተኛ ቢሆንም የአውስትራሊያ የውሃማ ቀለም አሳሳል ስልታቸው በብዙ ሕዝብ በጣም የሚደነቅ እና ተወዳጅ በመሆኑ የሳሉት ስዕል በአጭር ጊዜ ወዲያውኑ ይሸጥላቸዋል።

እሳቸው እና ባለቤታቸው በአውስትራሊያ ዜግነት የተሰጣቸው የመጀመሪያዎቹ የአቦሪጂናል ተወላጆች ናቸው። ይህም ማለት መምረጥ፣ ሆቴል መግባት እና በፈለጉት ቦታ ቤት መገንባት ያስችላቸዋል ማለት ነው። የአልበርት የአውስትራሊያዊ ዜግነት ሌሎች ነባር አውስትራሊያዊያን ይህ መብት እንዳልነበራቸው ያመላክታል።

ሚሰታቸው ፍትሃዊ ያልሆነ እና ነባር ላልሆኑ አውስትራሊያውያንን ብቻ የሚደግፍ ዘረኛ ሕግ ተለውጦ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦችን እንዲያካትት አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

## ኢዲ ማቦ (1936–92)



ኢዲ ኮይኪ ማቦ ቃል አቀባይ እና ሀገር በቀል የመሬት ይዞታ የመብት ተሟጋች ነበሩ። በቶረስ የባሕር ወሽመጥ የመሪያም ሕዝቦች መሬት ይዞታ ስር በምትገኘው በማርይ ደሴት ተወለዱ።

ከሕፃንነታቸው ጀምረው የትኛው ዛፍ እና ቋጥኝ በትክክል የቤተሰባቸውን የመሬት ይዞታ ድንበር እንደሚከልል ያስቡ ነበር።

ለብዙ አመታት ኢዲ መሬቱ የቤተሰባቸው ሳይሆን በአውስትራሊያ ሕግ መሰረት የዘውዳዊያን መሬት መሆኑን አያውቁም ነበር። ቁጣቸውን ወደ ተግባር በመለወጥ እና የማርይ ደሴት ሕዝብን በመወከል ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱት።

ከብዙ ዓመታት በኋላ የኢዲ ጉዳይ በ1992 ከበፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን ረታ። የአቦሪጂናል ሕዝቦች መሬታቸውን በተመለከተ ታሪካዊ እና ቀጣይነት ያለው ባህላዊ ትስስር እንዳላቸው ማረጋገጥ፣ ጥያቄ አቅርበው ካልነበረ ደግሞ የባለቤትነት ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችሉ የማቦ ውሳኔ ያዛል። ይህ ውሳኔ ለመጀመሪያዎቹ የመሬት ባለቤቶች ሰፊ መሬት እንዲመለስላቸው አስችሏል።

ኢዲ ማቦ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች የመሬት ባለቤትነት መብት ለማስገኘት በፈፀሙት ጀግንነት ሲታወሱ ይኖራሉ።

# የተለያየ ባህል ያላቸው ማህበረሰቦች ሰደት

በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ እያደገ የመጣው እንቅስቃሴ ብዙ ኤስያዊያን፣ ክርስቲያኖች እና ሌሎች ቡድኖችን ጨምሮ 'የአውስትራሊያ የነጮችፖሊሲ' እንዲያበቃ ተመኝቷል፡፡

መንግስት የቃል መመዘኛ ፈተና በ1958 ያስቀረ ሲሆን በ1966 የተመረጡ አውሮፓዊ ያልሆኑ እና ልዩ ሙያ ያላቸው ኤስያዊያን ስደተኞችን አውስትራሊያ መቀበል ጀመረች፡፡ በመጨረሻም አውስትራሊያዊያን የማንኛውም ሀገር ዜጋ በአውስትራሊያ በየትኛውም ቦታ የስደተኛ አቀባበል መርህ ስር ማካተቱን እውቅና ሰጡ፡፡

በ1973 የነጮች አውስትራሊያ ፖሊሲ አከተመ አውስትራሊያም የብዝሀነትን መንገድ መከተል ጀመረች፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መንግስት በዘር ላይ የተመሰረተ የስደተኛ መስፈርትን አስቀረ፡፡ ከቬትናም ጦርነት በኋላ በ1975 አውስትራሊያ ብዛት ያላቸው የኤስያዊያን ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች የተቀበለች ሲሆን በብዛት ከቬትናም፣ ከቻይና እና ከህንድ የመጡ ኛቸው፡፡

በጦርነት ከተጎዱ አገሮች የመጡ ብዛት ያላቸው ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጨምሮ ከ1945 ጀምሮ በሚልየን የሚቆጠሩ ሰዎች ለኑሮ ወደ አውስትራሊያ መጥተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአውስትራሊያ የሚገኙ ስደተኞች በዓለም ከሚገኙ አገራት ሁሉ የመጡ ናቸው፡፡

አውስትራሊያ ሁሉን አካታች የሆነ በስራ ላይ ያለ ፖሊሲ አላት ይህም ሲባል የየትኛውም ዘር፣ ጎሳ፣ ወይም ባህል አባል የሆነ ግለሰብ የማህበረሰቡ አንድ አካል እንደሆነ ይሰማዋል እንደ ማለት ነው፡፡ ይህ ፖሊሲ የመንግስትን ፖሊሲ ጨምሮ በሁሉም የአውስትራሊያ ማህበረሰብ ሁኔታ ላይ ተፈፃሚነት አለው፡፡ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ባለው የስርዓት ትምህርታችን ላይ ይንፀባረቃል፤ በማንኛውም የስራ ቦታም ይተገበራል፡፡

የማንኛውም ግለሰብ መብት ከመድልዎ ነፃ እና እኩልነት በተመላበት መንገድ እንዲስተናገድ በአውስተራሊያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና በየክፍለ-ሀገሩ እና ግዛቶች በሚገኙ ፀረ-መድልዎ ድርጅቶች ይተገበራል፡፡ የዘር መድልዎ በሕዝብ ዘንድ በህግ የተከለከለ ወንጀል ነው፡፡

አውስትራሊያ ስምምነት እና ተቀባይነት ያለው ብዝሀነትን የምታስተናግድ አገር ሆናለች፡፡ ስደተኞች፣ ነባር አውስትራሊያዊያን እና ማንኛውም አውስተራሊያ የተወለደ ግለሰብ ነፃነት ተሰምቶት ግቡን በሰላም የሚፈፅምባት አገር ነች፡፡

## ዶ/ር ቪክቶር ቻንግ (1936-91)

ዶ/ር ቪክቶር ቻንግ በጣም ታዋቂ ከሆኑ የልብ ቀዶ ሐኪሞች አንዱ ነበሩ፡፡ ቪክቶር ፒተር ቻንግ ያም ሂም በ1936 በቻይና ተወለዱ በ15 ዓመታቸውም ወደ አውስትራሊያ መጡ፡፡

በሲድኒ በሚገኘው ቅዱስ ቪንሰንት ሆስፒታል ሰርተዋል በ1984 ደግሞ የመጀመሪያውን የልብ ንቅለ ተከላ ሕክምና የሚሰጥበት ማዕከል አቋቋሙ፡፡ ለሰሩት ድንቅ ስራ እውቅና እና ትልቁ የክብር ሽልማት በ1986 ተበርክቶላቸዋል፡፡

ልብ የሚለግሱ ሰዎች መጥፋቱ ቪክቶርን ያሳስባቸው ስለነበረ የሰው ሰራሽ ልብ ንድፍ መንደፍ ጀምረው ስራውን ሊያጠናቅቁ በተቃረቡበት ወቅት በአሰቃቂ ሁኔታ በ1991 ተገደሉ፡፡

ለእሳቸው መታሰቢያነት አንድ አዲስ የምርምር ማዕከል ተመሰረተ፡፡ በሙያዊ ብቃታቸው፣ ቀናነታቸው እና ፈጠራቸው ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡



# ለማጠቃለል

እነዚህ ገፆች የእኛ የአውስትራሊያዊያንን ታሪክ ምን እንደሚመስል በትንሹ ይገልፁላችኋል፡፡ የአውስትራሊያ ዜጋ እንድትሆኑ መልካም ፈቃዳችን ሆኖ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ በሆነችው ሀገራችን ሙሉ ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡

እንደ አንድ ዜጋ ከሌሎች የአውስትራሊያ ዜጎች እኩል ተጠቃሚነት እና ኃላፊነት እንዲያገኙ እንዲሁም የአውስትራሊያ ማሕበረሰብ ሙሉ አባል ይሆናሉ፡፡ የአውስትራሊያን መፃኢ እድል ለመቅረፅ በሚደረገው ብሔራዊ ፕሮጀክት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ኃላፊነትዎን ይወጣሉ፡፡

# የቃላት ፍች

**አምባሳደር**
አገርን ወይም ተግባርን የሚወክል ወይም የሚያስተዋውቅ ሰው

**ቦርድ**
ውሳኔ እንዲወስኑ የተመረጡ የግለሰቦች ስብስብ ለምሳሌ አንድ ድርጅት እንዴት እንደሚመራ

**አዳሪ ትምህርት ቤት**
ተማሪዎች ትምህርት በሚሰጥባቸው ወራት ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ የሚማሩበት እና የሚኖሩበት ትምህርት ቤት

**ቁጥቋጥ**
በተፈጥሮ ይዘቱ ላይ የሚገኝ የአውስትራሊያ የገጠሩ ክፍል

**የዳልጋ ከብት ጣቢያ**
የዳልጋ ከብት የሚረቡበት ትልቅ የእርሻ ቦታ

**ሕገመንግስት**
በፅሁፍ የተገለፀ መደበኛ መብት እና ግዴታ

**የጋራ መነሻ /መሰረተ ሃሳብ**
ተመሳሳይ ፍላጎት

**የግዴታ ምልምል ወታደር**
ወታደር ለመሆን ፍላጎት ባይኖረውም በጦርነት ጊዜ ወታደር የሚሆን

**ዘውዳዊ መሬት**
የመንግስት የሆነ መሬት

**ስርዓተ ትምህርት**
በአንድ የትምህርት ዓይነት የሚጠና ትምህርት እና ርዕስ

**ችግረኛ/ምስኪን**
ገንዘብ የሌለው ወይም እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንደሚቻል የማያውቅ

**ድጂሪዶ**
ውስጡ ክፍት ከሆነ ረጅም ቅርንጫፍ የሚሰራ የአውስትራሊያ አቦሪጂናል ሕዝቦች የሙዚቃ መሣሪያ

**ሚዛናዊነት/ፍትሃዊነት**
ሕግን የተከተለ እና አግባብነት ያለው፤ ከአድልዎ የፀዳ እና በታማኝነት ሕብረተሰብን ማገልገል

**የጦር ጉዳተኛ**
ወታደራዊ አገልግሎት ሲሰጡ በጦርነት ወይም ውጊያ ምክንያት የሞቱ

**ማነፅ**
ማነፅ ወይም መፍጠር

**የሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት**
በአንድ አገር በአንድ ዓመት ውስጥ የተመረተ ምርት እና አገልገሎት ዋጋ

**የሙቀት ሞገድ/ሚራጅ**
ከሁለት ቀን በላይ የሚቆይ በጣም ሞቃታማ የሆነ የአየር ንብረት

**ከፍተኛ የሀገር ክህደት**
ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ጥሰት፣ መንግስት ግልበጣን ያካትታል

**ድንቅ**
በጣም የታወቀ እና ወካይ አምሳያ

**አንድን አካባቢ የሚወክል የአሳሳል ዘዴ**
የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች የሚወክል ልዩ ጥበብ

**ተወላጅ/ሃገር በቀል**
የአውስትራሊያው የአቦሪጂናል እና/ወይም ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች

**ሰፊ መሬት**
ሰፊ ቦታ ያለው መሬት

**ወሳኝ ጊዜ**
ታሪካዊ ወሳኝ የድርጊት ጊዜ

**የተወላጁ መብት**
በአውስትራሊያ የሕግ ማዕቀፍ ስር ለመሬት እና ውሃ የሚሰጥ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ ባህላዊ መብት

**አፈ ታሪክ**
ባለፉት ዘመናት የተከናወኑትን የሚያስታውስ በሰዎች የሚነገር

**ፈር ቀዳጅ /መስራች**
ከመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች አንዱ የሆነና በቅኝ ግዛት ሰፈራ ወቅት ውጤታማ የሆነ ስራ የሰራ

**ፖለቲካዊ ውክልና**
በአስተዳደሩ የሚወከል የምክር ቤት አባል

**የፍርድ ውሳኔ**
በዳኛ የሚወሰን ቅጣት ለምሳሌ ጥፋት ሰርቶ ለተገኘ ግለሰብ ለተወሰኑ ጊዜያት በእስር ቤት መቆየት

**ደመወዝ መደልደል**
ሰራተኞች ለሰሩት ስራ ምን ያህል ሊከፈላቸው እንደሚገባ መወሰን

**ማሕበራዊ ማሻሻያ**
ስርነቀል ለውጥ ሳይሆን ቀስ በቀስ ለማሕበረሰቡ ማሻሻያ ማድረግ

**መንግስታዊ ስርዓተ ቀብር**
ለሀገሪቱ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ዜጎች ክብር በመንግስት የሚሸፈን የቀብር ማስፈጸሚያ ክፍያ

**ምሽግ**
በእንጨት የሚሰራ የመከላከያ ጉድጓድ

**እረኞች**
ተቀጥረው የዳልጋ ከብት የሚጠብቁ

**አመፅ**
የሰራተኞች የስራ ማቆም አድማ፤ ለምሳሌ በስራ ወይም ክፍያ ሁኔታ ማመፅ

**የምርጫ መብት**
በሕዝባዊ ምርጫ ላይ ድምፅን የመጠቀም መብት

**መሓላ**
በመንግስታዊ መስሪያቤት ተቀባይነት ለማግኘት የሚፈፀም መደበኛ ስነ ስርዓት

**የስራ ድርሻ**
መደብ ወይም የስራ ደረጃ

# ለተጨማሪ መረጃ

## የአውስትራሊያ ዜግነት

እንዴት የአውስትራሊያ ዜጋ መሆን እንደሚቻል አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ካስፈለግዎ www.citizenship.gov.au. የሚለው ድህረ-ገፃችንን ይጎብኙ

## አውስትራሊያ

አውስትራሊያን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በአካባቢዎ በሚገኘው ቤተ መፅሀፍት ማግኘት ይችላሉ። የሚከተሉት ድህረ-ገፆች ጠቃሚ መረጃዎችን ይዘዋል፥

- አውስትራሊያን አስመልክቶ www.australia.gov.au
- የአውስትራሊያ አጭር መግለጫ www.dfat.gov.au

## የአውስትራሊያ መንግስት ፕሮግራም እና አገልግሎት

የአውስትራሊያ መንግስት ፕሮግራም እና አገልግሎት አስመልክቶ ለበለጠ መረጃ www.australia.gov.auን ይጎብኙ

## የፌደራል ወይም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል

በአካባቢዎ ከሚገኘው በግዛቱ የፌደራል ወይም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት የአውስትራሊያ መንግስት ፕሮግራም እና አገልግሎት አስመልክቶ የተለያዩ መረጃዎች ይኖሩታል።

የፌደራል እና የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ዝርዝር በwww.aph.gov.au አለ።

## የአውስትራሊያ መንግስት ድርጅቶች

የአውስትራሊያ መንግስት ድርጅቶችን አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በመፅሐፉ ላይ እንደተመለከተው የሚከተሉትን ድህረ-ገፆች ይጎበኙ

- የኣውስትራሊያ መከላከያ ሃይልwww.defence.gov.au
- የኣውስትራሊያ የኤሌክትሪክ ኮሚሽን www.aec.gov.au
- የኣውስትራሊያ ፌደራል ፖሊስ www.afp.gov.au
- የኣውስትራሊያ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን www.humanrights.gov.au
- የኣውስትራሊያ ስፖርት ኮሚሽን www.sportaus.gov.au
- የኣውስትራሊያ የታክስ ቢሮ www.ato.gov.au
- የኣውስትራሊያ የጦር መዘክርwww.awm.gov.au
- የኣውስትራሊያ መጠባበቂያ ባንክ www.rba.gov.au

# መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

መንግስታዊ ስላልሆኑ ድርጅቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በዋናው የመረጃ ምንጭ መፅሃፍ ላይ ማግኘት ይችላሉ በተጨማሪም ቀጥሎ የተመለከቱትን ድረ ገፆች ይጎብኙ

- የብራድማን ፋውንዴሽን ኣውስትራሊያ www.bradman.com.au
- ሃምሊን ፊስቱላ www.hamlinfistula.org
- ሮያል ፍላይንግ ዶክተር ሰርቪስ ኦፍ ኣውስትራሊያ www.flyingdoctor.org.au
- ስኩል ኦፍ ዘ ኤየር www.schoolair-p.schools.nsw.edu.au
- ስኖው ማውንቴይንስ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኣውቶሪቲ www.snowyhydro.com.au
- ዘ ፊሬድ ሃሎውስ ፋውንዴሽን www.hollows.org
- ዩኔስኮ ወርልድ ሄሪቴጅ ሴንተር whc.unesco.org
- ዩናይትድ ኔሽንስ www.un.org
- ቪክቶር ቻንግ ካርዲያክ ሪሰርች ኢንስቲትዩት www.victorchang.edu.au
- ቮሉንቲሪንግ ኣውስትራሊያ www.volunteeringaustralia.org

# ሌሎች

በሚከተሉት ርእሶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተሉትን ድረ ገፆችን ይጎብኙ።

- የኣውስትራሊያ ህገ መንግስት www.aph.gov.au
- የዓመቱ ኣውስትራሊያዊ ሰው ሽልማት www.australianoftheyear.org.au
- ‘ወደ ሃገር እናምጣቸው/Bringing them home’ ሪፖርት www.humanrights.gov.au
- የጋራ ብልፅግና ፓርኮችና ጥብቅ ደኖች www.environment.gov.au
- የበይነመረብ ደህንነት www.esafety.gov.au
- የቤትና የቤተሰብ ጥቃት ህገ ወጥ ነው። የሀገር ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከት/ጥቃት ድጋፍ www.respect.gov.au, www.1800respect.org.au, www.dss.gov.au/women/help-is-here-campaign
- እውቅ ኣውስትራሊያኖች የኣውስትራሊያ የታሪክ መዝገበ ቃላት adb.anu.edu.au
- እስከ ኣሁን ድረስ ለፓርላማ የቀረቡ ዝርዝር የህግ ረቂቆች www.aph.gov.au
- የኣውስትራሊያ ፓርላማ www.aph.gov.au
- የፓርላማ የትምህርት ቢሮ www.peo.gov.au
- የህዝብ በዓላት www.australia.gov.au
- ዘረኝነት humanrights.gov.au
- ለኣውስትራሊያ ኣቦርጅኖችና ቶረስ የባረ ሰላጤ ደሴተኞች የተደረገ ይቅርታ www.australia.gov.au

# እውቅናና ምስጋና


### ለግብርና ሚኒስቴር ክብር ይግባውና ውሃና ኣካባቢ የሚሉት ምስሎች ቀጥሎ ቀርበዋል፥

p50 የታዝማኒያ ጫካዎች

### ቀጥሎ ለሚቀርቡ ምስሎች ለሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እናመሰግናለን፥

p5 የዜግነት በዓል ኣልበርት ኣደራሽ ካንቤራ

p5 የኣውስትራሊያ የዜግነት የምስክር ወረቀት

p11 የማጨስ ስነ ሰዓት ካንቤራ

p34 ኣንድ ቤተሰብ በኣውስትራሊያ የዜግነት ስነስርዓት ካንቤራ

### ቀጥሎ ለሚቀርቡ ምስሎች ለብሄራዊ ቤተ መዛግብት ኣውስትራሊያን እናመሰግናለን፥

p51 ህፃናት በበጎች በረት NSW – በSchool of the Air, በ 1962 ዓ/ም የተኣሳ ፎቶግራፍ (ref: A1200:L42511)

p60 ዲክ ስሚዝ የሲቪል የበረራ ባለስልጣን ሊቀመንበር በ1991(ref: A6135:K23/5/91/1)

p65 የኣቤል ታዝማን ካርታ በ ኒው ሆላንድ 1644 (ref: A1200:L13381)

p68 የወርቅ ጥድፊያ / the gold rush ታሪካዊ ስእል በኣውስትራሊያ በ1851 (ref: A1200:L84868)

‘ኣፍጋን/Afghan’ የግመል ጎታች በበረሃማው ኣውስትራሊያ (ref: A6180:25/5/78/62)

p77 ሰር ኤድዋርድ ‘ዊሪ/Weary’ ዳንሎፕ በቢሮኣቸው በ1986 (ref: A6180:1/9/86/12)

p78 የኣውሮፓ ስደተኞች በኣውስትራሊያ፣ የጣሊያን የስኳር ኣገዳ ቆራጮች በፍላሚንያ ጀልባ። በኬንስ 1955 (ref: A12111:1/1955/4/97)

### ቀጥሎ የተመለከቱት ሰእሎች ለኣውስትራሊያ ብሄራዊ ቤተ መፃህፍትን እናመሰግናለን፥

P53 የጁዲ ራይት ፎቶግራፍ በ 1940ዎቹ የታተመ (ref: nla.pic-an29529596)

p65 ለመጀመሪያ ጊዜ በሲድኒ ሰርጥ የደረሱ መርከቦች ጥር 27 ቀን 1788, ከጆን ኣልኮት የተገኘ ከ1888 – 1973 (ref: nla.pic-an7891482)

p66 Pየካሮሊን ቺዝም ፎቶግራፍ, ከ1804 – 1852 በቶማስ ፌርላንድ የታተመ። (ref: nla.pic-an9193363)

p71 የካተሪን ሄለን ስፔንስ ፎቶግራፍ በ1890ዎቹ የታተመ (ref: nla.pic-an14617296)

p74 ጆን ሲምሰንኪርክ ፓትሪክና ኣህያው ጋሊፖሊ በ1915 (ref: nla.pic-an24601465)

p76 የሰር ቻርለስ ኤድዋርድ ኪንግስፎርድ ስሚዝ ፎቶግራፍ በ1919 ና 1927 የታተመ (ref: nla.pic-vn3302805)

p81 Portrait of የኣልበርት ነማቲጂራ ፎቶግራፍ በሄርማንስበርግ ግዳጅ ላይ ሰሜናዊ ክልል/Northern Territory በ1946 ወይም 1947በኣርተር ግሩም የታተመ (ref: nla.pic-an23165034)

### የሚከተሉትን ምስሎች ለሰጠን ለiStock እናመሰግናለን፥

ሽፋን የሚሞሳ ምንጭ ኣበባዎች /Mimosa imosa spring flowers, ©iStockphoto.com/ST-art (ref: 1135566007)

p6 ካንጋሩና ግልገሏ በ ላኪ የባህር ዳርቻ ምዕራብ ኣውስትራሊያ ©iStockphoto.com/NeoPhoto (ref: 1142608453)

p9 የሂዩም ሃይቅ Lake Hume, ቪክቶሪያ ©iStockphoto.com/tsvibrav (ref: 675826394)

p15 የኣውስትራልያ ጥቁር መረግድ/ኦፓል ©iStockphoto.com/Alicat (ref: 173691056)

p17 የኣውስትራሊያ ባንዲራ, ©iStockphoto.com/davidf (ref: 471630390)

p19 ህብረ ብሄራዊ የልጃገረዶች ኣንደኛ ደረጃ ት/ቤት ©iStockphoto.com/FatCamera (ref: 877714382)

p23 የኣውስትራሊያ ፓርላማ ካንቤራ ©iStockphoto.com/felixR (ref: 157193181)

p33 የህዝብ ስብስብ ©iStockphoto.com/davidf (ref: 913541808)

p36 የውሳኔ መዶሻና የፍትህ ሚዛን ©iStockphoto.com/studiocasper (ref: 1004781908)

p37 የተለያዩ ቡድኖች ©iStockphoto.com/SolStock (ref: 1203934273)

p39 Green Wattle Creek fire NSW, Australia, December 2019, ©iStockphoto.com PetarBelobrajdic (ref: 1198579743)

p47 በእጅ የተሳለ መለከት/ዲጂሪዱ /didgeridoos, ©iStockphoto.com/lore (ref: 185011099)

p48 ቦንዳይ የባህር ዳርቻ ሲድኒ ©iStockphoto.com/Edd Westmacott (ref: 91095176)

p49 ሲድኒ ኦፕራ ሃውስ ኒው ሳውዝ ዌልስ ©iStockphoto.com/slowstep (ref: 607986870)

p50 ኡሉሩ -ካታ ቱጂታ ብሄራዊ ፓርክ , ሰሜናዊ ክልል/Northern Territory, ©iStockphoto.com/bennymarty (ref: 1184425004)

p63 ኡሉሩ ሰሜናዊ ክልል/ Northern Territory, ©iStockphoto.com/simonbradfield (ref: :539027478)

p64 የአቦሪጅኖች የአለት ስነ ጥበብ – ሳራቶጋ ዓሳ/Saratoga fish, ©iStockphoto.com/Alpen Gluehen (ref: 2761924)

p75 የአውስትራሊያ የጦር ሜዳ ውሎ መታሰቢያ ግድግዳዎች፣ካንቤራ /Walls of Australian War Memorial, ካንቤራ ©iStockphoto.com/ Matt Palmer (ref: 1125736631)

## ቀጥሎ ያሉትን ፎቶግራፎች ለሰጠን ለShutterstock እናመሰግናለን፥

p7 አገር በቀል ጨፋሪዎች በትውልድ አገር ፌስቲቫል ሲድኒ ©shutterstock.com/PomInOz (ref: 345113882)

p21 ድምፅ ሰጭ ©shutterstock.com/Nils Versemann (ref: 446229916)

p31 የአውስትራሊያ ከፍተኛ ፍርድቤት ©shutterstock.com/Greg Brave (ref: 1051621895)

## ሊሎች ፎቶግራፎችን የሰጡንን ቀትጥሎ የተዘረዘሩትን የትሊያዩ ድርጅቶችና ሰዎችን እናመሰግናለን

p24 Cአውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ህገመንግስት፤ ህግ 1900: ዋና የህዝብ መዝገብ ቅጂ፣ በስጦታ የቀረቡ ምስሎች፣ የፓርላማው የስነ ጥበብ ስብስቦች፣ የፓርላማው የመምሪያው አገልግሎቶች ካንቤራ ACT

p40 የሀርድና የማክዶናልድ ደሴቶች ምስሎች ከአውስትራሊያ የአንታትርቲክ ክፍል የተገኙ ናቸው፡፡© Commonwealth of Australia, photograph by L. E. Large (ref:1892A2)

p52 የሰር ዶናልድ ብራድማን ፎቶ ከብራድማን የክሪኬት ሙዝየም የተገኘ ሰር የሰር ዶናልድ ብራድማን የአውስትራሊያ የውድድር ኮፍያ አድርገው ከ1931-32 በነበረው የአውስትራሊያ ውድድር የተነሱት፡፡

p54 ዶ/ር ፊዮና ዉድ ኤም የአውስትራሊያ ብሔራዊ ቀን ምክር ቤት መልካም ሰው ጀግና

p55 ፕሮፌሰር ፍሬድ ሃሎውስ በፍራንክ ቪየሊ ተነስቶ ከፍሬድ ሃሎውስ ፋውንዴሽን የተገኙ፡፡r

p56 ዶ/ር ጀምስ ሙኬ ኤም የዓመቱ አውስትራሊያዊ ሰው ሽልማት ጀግና

p56 ፐሮፌሰር ሚኬል ሲሞንስ ብሔራዊ የአውስትራሊያ ቀን ምክር ቤት ጀግና

p61 ዶ/ር ካትሪን ሃምሊን AC ከ ሃምሊን ፊስቱላ መልሶ ማቋቋምና እርዳታ የገንዘብ ተቋም የተገኘ፡፡

p71 የሎርድ ላሚንግተን በፌደሬሽን ቀን ለህዝቡ ንግግር እያደረጉ የተነሱት ብሪዝቤን 1901, ፎቶግራፉ የተነሳው በ H.W. Mobsby ሲሆን የተገኘው ደግሞ ከኩንስላንድ የመንግስት ቤተ መፃህፍት ነው፡፡ (ref: 47417)

p72 ኢዲዝ ኮዋን የአውስትራሊያ ብሔራዊ ሙዚየም ጀግና

p73 ዶሮቴ ሜኬላር የNSW መንግስት ቤተመፅሐፍ ጀግና

p76 የሾርባ ማድ ቤት /Soup kitchen /ፎቶ የተገኘው በኒው ሳውዝ ዌልስ የመንግስት ቤተመፃህፍት (Mitchell Library). የትምህርት ቤት ህፃናት ሰልፍ ለነፃ ሾርባና ለቁራጭ ዳቦ ፈቃድ ሰሜናዊ ቤልሞር የህዝብ ትምህርት ቤት NSW, ነሃሴ 2 ቀን 1934, በሳም ሁድ የተነሳ (ref: H&A 4368)

p77 በኮኮዳ መንገድ የቆሰለ ወታደር ፎቶ ከአውስትራሊያ የጦር መታሰቢያ የተገኘ (ref: 014028)

p81 አኢዲ ማቦ ፎቶግራፍ በቤርኒታና ጋሊ ማቦ ፈቃድ የተራባ

p82 ዶ/ር ቪክቶር ቻንግ ፎቶ ከቪክቶር ቻንግ የልብ ህክምና የምርምር ተቋም የተገኘ፡፡

# ማስታወሻ

